
ኢትዮ - ትረካ
እንኳን ደና መጡ ! !
@ethio_terka
TAFT PHOTOGRAPHY

ዓይን ሲያየው ይህ ቀጠን ብሎ ከቁመቱ ዘለግ ያለና የወታደር ልብስ የሚለብሰው ሰው በዓይነ-ቁራኛ ይከተለዋል:: ከዓይኑ እስኪሰወረ ድረስ አተኩሮ ከመመልከትና መሴይ ማንደላይንን ከማጤን አይቆጠብም:: ግምባሩንም እየቋጠረ «ይሄ ሰው ማነው?» በእርግጥ ከአሁን በፊት አይቼዋለሁ? የት ነው የማውቀው? ሰው ሁሉ ያደንቀዋል? ይወደዋል፤ እኔ ግን እጠራጠረዋለሁ» የሚል ይመስል አጠገቡ ሰው ሳይኖር ከንፈሩን ያንቀሳቅሳል:: መሴይ ማንደላይንን ባየ ቁጥር ከሃሳብ ጋር ሙግት መግጠሙን ያስታውቅበታል::

ሰውዬው ከስተርተር የሚል ዓይነት ስለነበር እንኳን በዓይነ-ቁራኛ ተከትሎ ለአንድ አፍታ ቢያይም «ይሄ ሰውዬ ከኔ ነገር አለው?» የሚያሰኝ ዓይነት ፊትና አመለካከት ያለው፤ ሳይወዱ በግድ ጭንቀትን ከልብ ውስጥ በማሳደር የሕሊና መረበሽን አንጎል ውስጥ የሚፈጥር ዓይነት ሰው ነበር::

ስሙ ዣቬር ይባላል:: ፖሊስ ነው:: ተራ ፖሊስ ሳይሆን የከተማው ፖሊስ አዛዥ ነው:: መሴይ ማንደላይን ወደ ከተማው ሲመጣ ከዚያ አልነበረም::

አንዳንድ የፖሊስ መኮንኖች የተለየ መልክ አላቸው:: አንዳንዱ ደማቸው ውስጥ ከእልቅናቸው ጋር የተቀራኘ ክፋት ስለመኖሩ ገጽታቸው ላይ ይታያል:: ዣቬር የዚህ ዓይነት ገጽታ ቢኖረውም በውስጡ ግን ክፋት የተቀበረበት ዓይነት ልው ነበር ለማለት አያስደፍርም:: እስር ቤት ነው የተወለደው:: እናቱ ደግሞ ጠንቋይ ነበሩ:: አባቱ የወህኒ ቤት ሠራተኛ ስለነበሩ ሁልጊዜም ሕብረተሰቡ የእነርሱን ቤተሰብ ከማኅበራዊ ኑሮ ያገለለ ይመስላቸው ስለነበር ዣቬር ቀበጸ-ተስፋ ያጠቃዋል:: የሰውን ልጅ ከሁለት ከፍሎ ነው የሚያየው:: አንደኛው ወገን ሕብረተሰብን የሚያጠቃ ሲሆን ሌላው ወገን ከዚህ ጥቃት የሚከላከልለት ክፍል ነው:: ዣቬር በሥነ ሥርዓትና በቅንነት በጣም ያምናል:: ጎሳውን ግን ይጠላል:: ፖሊስ ለመሆን ፈልጎ ነው የፖሊስ ኃይል አባል የሆነው:: በሥራው ምስጉን ፖሊስ መሆኑ ስለተረጋገጠ በአርባ ዓመቱ ከፍተኛ የማዕረግ እድገት አግኝቶ የክፍል አዛዥ ሆነ:: በወጣትነት ዘመኑ ደቡብ ክፍለ ሀገራት ውስጥ ከሚገኝ ወህኒ ቤት እንዲሠራ ይመደባል::

አፍንጫው እንደ ቀትር እባብ ቀጥ ያለ ሲሆን ራሱን ከግራና ከቀኝ በጣም አሳድጎት ጉንጮቹን ሸፍኖበታል:: ዣቬር ድንገት የሳቀ እንደሆነ ስስ ከንፈሮቹ ተገልጠው ጥርሶቹን ብቻ ሳይሆን የሚያሳዩት ድዶቹንም ጭምር ነው:: ግን ብዙ ጊዜ መሳቁ ተርገን እንጂ ሳቅ አያውቅም:: ከአፍንጫው ግራና ቀኝ የተሸበሸበ ሥጋ አለው:: ይህም ሲቆጣ የአደን ውሻን፣ ሲስቅ ደግሞ ነብርን ያስመስለዋል:: ከዚህ በተረፈ ጭንቅላቱ ትንሽ፣ አገጩ ሰፊ፣ ፀጉሩን



ወደፊት እያበጠረው ግምባሩ እስከ ቅንድቡ በፀጉር የተሸፈነ፤ ጨለማ ፊት ያለው፤ ፊቱ የሚያርገበግብና የክፋት አሊቃ ሰውነት ያለው ሰው ነው::

ይህ ሰው በሁለት ዓይነት አመለካከቶች የተገነባ ነበር:: በመሠረቱ አስቦቹ ምንም ዓይነት ስሁት የሌለባቸው ቀላል አመለካከቶች ሲሆኑ ዣቬር ግን በጣም ስለጋነናቸው እንደ ክፉ ነገር ነበር የሚያያቸው:: እነርሱም ባለሥልጣንን ማክበርና ሕግ የሚጥሱትን መጥላት ናቸው:: በእርሱ አመለካከት ሲብራራ፣ ግድያና ማንኛውም ወንጀል መፈጸም ማለት ሕግን መጣስ ማለት ነው:: በማንኛውም የሥራ መስክ የተሰማሩ የመንግሥት ሠራተኞች ማለት ከአገር መሪ ጀምሮ እስከ ተራ ወታደርና ተላላኪ ድረስ የእርሱን እምነት መቀበል እንዳለባቸው ያምናል:: በእርሱ አመለካከት ሕግ የሚጥሱትን ሁሉ ተከታትሎ ማጥፋትና ማስወገድ ተግባር እርምጃ ነው:: ሕግ የሚጥሱትን ከመጠን በላይ ይጠላል:: ማንንም ሳይለይ ሕግን ማስከበር ለእርሱ ትልቅ ቁም ነገር ነው::

«በአንድ በኩል» ይላል ዣቬር፤ «የመንግሥት ባለሥልጣንን ማታለል አይቻልም፤ ሕግ አስከባሪ ዳኛ ደግሞ ፈጽሞ አይሳሳትም:: በሌላ በኩል ደግሞ» ይላል፤ «መዳኛ ከሌለው አዘቅት ውስጥ ከተዘፈቁ ክፉ ሰዎች በጎ ተግባር አይጠበቅም::»

«ሰው የሠራው ሕግ መጣስ የለበትም» ብለው የሚያምኑ የአንዳንድ ወግ አጥባቂዎችን እምነት ይከተላል:: ከተጠራጠረ እንደ ጦር የሚወጋውን ዓይኑን ሰው ላይ እንዲተክል የሚገፋፋው ይህ እምነቱ ነበር:: ይህም በመሆኑ «ነቅቶ መጠበቅ» በሚል ፍልስፍና ሕይወቱን ያነፃል:: በዚህም የተነሳ ሕሊናው ሕግን በማስከበር፣ እምነቱ የእለት ተግባሩን በመከታተል ላይ ያተኮረ ሲሆን ቁሶች ለቅዱሱ እንደሚሯሯጡ ሁሉ እሱም ለስለላ ተግባር ይሯሯጣል::

ይብላኝለት እርሱ መዳፍ ውስጥ ለሚወድቅ:: አባቱ ከእስር ቤት ሲያመልጥ ቢያየው ሮጦ ሄዶ ያሲዘዋል:: እናቱ አንድ ጊዜ ቲኬት ስታጭበረብር ስላገኛት አሳልፎ ሰጥቶአታል:: ዣቬር ተመሳሳይ የሆነ ሥራ በሚሠራበት ጊዜ ትክክለኛ ነገር እንደፈጸመ ሰው መንፈሱ ይረካል:: ሕይወቱ በብቸኝነትና በግላዊነት የተሞላ ሲሆን ከንለማዊ ምቾት የራቀ ነበር:: የእርሱ ደስታ ወንጀለኞችን ተከታትሎ ማደን እንጂ ዳንኪራ መርገጥ ወይም ሙዚቃ ማዳመጥ አልነበረም::

ዣቬር ማለት ይህ ሲሆን አሁንም ዓይኑን ከመሴይ ማንደላይን አላነሳም፤ በጣም ይጠራጠረዋል:: ግን የተጨበጠ ማስረጃ ሊያገኝ አልቻለም:: በመጨረሻ በክፉ ዓይን እንደሚያየው መሴይ ማንደላይን ደረሰበት:: ሆኖም

ከምንም አልቆጠረውም:: ዣቬር ማን እንደሆነ ለማወቅ ፈልጎ ጥያቄ አልጠየቀውም:: ለማንኛውም ብዙም አላተረበውም፤ ብዙም አልሸሸጉ:: በየጊዜው ሲያፈጥበት እያየ እንዳላየ ሆኖ ያልፈዋል:: ሌሎችን በሚያደበትን ደግነት በተሞላበት አንደበት በረጋ መንፈስ ዣቬርንም ያነጋግረዋል:: የመሴይ ማንደላይን ሁናቴ ዣቬርን በይበልጥ ግራ አጋባው:: ሆኖም አንድ ቀን የዣቬር ሁኔታ መሴይ ማንደላይንን ያስቆጣዋል:: ነገሩ እንዲህ ነበር::

አንድ ቀን መሴይ ማንደላይን ከአንዲት መንደር ውስጥ ከወዲያ ወዲህ እያለ ይንሸራሸራል:: ጩኸት ሰምቶ ዞር ሲል ሰዎች ተሰብስበው ያያል:: ወደ ሥፍራው ቢሄድ ደብተራ ፎሸለማ የተባሉ ሽማግሌ ወድቀው እቃ የጫነ ጋሪ ተጭኖአቸዋል:: ፈረሱም ወድቆ እግሩ ስለተሰበረ መንቃ እንዳቃተው ሁሉ ሽማግሌውም ጋሪው ተጭኖአቸው ሊንቀሳቀሱ አልቻሉም:: ጋሪው ላይ መጠነኛ ጭነት ስለነበረ ሽማግሌው የጣር ያህል ነበር የተጨነቁት:: ሰዎች ተሰብስበው ጭነቱን ብድግ አድርገው ሊያላቅቋቸው ቢሞክሩም አልሆንላቸውም:: ዋጋ የሌለው ሙከራ የአንዳንዱ አያያ የአላዋቂ ሲሆን የአንዳንዱም አያያዝ ለማስመሰል ያህል ብቻ ነበር:: ሽማግሌው ትንፋሽ አጥሯቸው ሊሞቱ ሆነ:: መፍትሔው ከሥር ገብቶ ጋሪውን ብድግ ማድረግ ነበር:: ከጋሪው ላይ ወጥቶ የተጫነውን ጭነት ለማራገፍ ከሞከሩ የባሰውን ሊጫንዋቸው ሆነ:: ከሥሩ ገብቶ በሸክም ብድግ ለማድረግ ለራ የሚያስፈራ ሆነ:: ስለዚህ ሁሉም ተፋጠጡ:: ዣቬር አደጋው እንደደረ መጥቶ ስለነበር የእቃ ማንሻ መሣሪያ እንዲመጣ ሰው ልኮአል::

መሴይ ማንደላይን ከሥፍራው ደረሰ:: ሕዝቡ መንገድ ለቀቀለት:: «እርዱኝ እባካችሁ» ብለው ሽማግሌው ጮኹ:: «የማነው ሳምራዊ ይህ ሽማግሌ የሚያድን?» ሲል መሴይ ማንደላይን ጠየቀ::

መሴይ ማንደላይን ዞር ዞር እያለ ተመለከተ::

«የእቃ ማንሻ መሣሪያ ያለው የለም?»

«ሰዎች ሊያመጡ ሄደዋል» አለ አንድ ሰው::

«ቶሎ ይደርሳሉ?»

«ፍሉቭ ከተባለ ሥፍራ ወደሚገኝ አንጥረኛ ነው የሄዱት:: መቼ ቢያንስ አንድ ሩብ ሰዓት ያህል ያቆያቸዋል::»

«ሩብ ሰዓት!» ሲል ጮኸ::

ሌሊቱን ሲዘንብ ስላደረ አካባቢው ጨቅይቶ ነበር:: ፈረሱ ተንሸራትቶ የወደቀበትም ሥፍራ እንደማጥ ዓይነት ስለነበር የጋሪው እግሮች በአንደ በኩል ከጭቃው ውስጥ እየዘለቁ ወደ ውስጥ ሰመጡ:: በዚህ ዓይነት



በአምስት ደቂቃ ጊዜ ውስጥ የሽማግሌው ወገብ ሊቀነጠስ ሆነ::

«ሩብ ሰዓት መቆየት አንችልም» አላቸው መሴይ ማንደላይን እዚያ የተሰበሰቡትን ሁሉ እያየ::

«ሌላ ምርጫ የለም::»

«ከሩብ ሰዓት በኋላማ ዋጋ የለውም:: ጋሪው እየሰመጠ መሆኑን አይታያችሁም እንዴ!»

«ምንም ማድረግ አይቻልም::»

«ስሙ» አለ መሴይ ማንደላይን፤ «አሁኑኑ ከሆነ ከእቃ መጫኛው ሥር ራስን ለማስገባት የሚያስችል በታ አለ:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ግን ይህ አይቻልም::» ስለዚህ አሁን ጥቂት ሰዎች ተንፏቅቀው ገብተው በጀርባቸው ጋሪውን ብድግ ማድረግ አለባቸው:: ይህ ከሆነ ሰውዬው በግማሽ ደቂቃ ውስጥ ይወጣሉ:: ማነው እስቲ ጎበዝ ሰውዬውን የሚያድን? መቶ ፍራንክ ይከፈለዋል::»

ሁሉም ዝም!

«ሁለት መቶ ፍራንክ» አለ መሴይ ማንደላይን::

የተሰበሰበው ሰው መሬት መሬት ያይ ጀመር::

«ከእዚያ ውስጥ ደፍሮ የሚገባ ሰው በጣም ጡንቸኛ መሆን አለበት:: ግን እኮ ያ ሰው ከዚያ በኋላ እንዴት ይወጣል፤ እዚያው ተጨፍልቆ ይቀራል እንጂ» አለ አንድ ሰው በመካከሉ::

«በሉ እባካችሁ! አራት መቶ ፍራንክ»

«አሁንም ዝም»

«ፈቃደኛነቱ እኮ አይደለም የጠፋው» አሉ አንድ ሰው::

መሴይ ማንደላይን ዞር ብሎ ሲያይ ዣቬርን አየው:: ከዚያ ለመኖሩ አልተገነዘበም ነበር:: ዣቬር ቀጠለ::

«ኃይል ነው የሚያስፈልገው:: ከዚያ ውስጥ የሚገባ ሰው ደፋርና እጅግ በጣም ጉልበተኛ መሆን ይኖርበታል:: ይህን የሚያህል የእቃ መጫኛ ጋሪ በጀርባው ተሸክሞ ለማንሳት የሚችል ምን ዓይነት ጉልበተኛ ነው?»

ከዚያ በኋላ ዣቬር መሴይ ማንደላይንን እንደልማዱ አፍጥጦ እያየው እያንዳንዱን ቃል ረጋ አድርጎ የሚከተለውን ተናገረ::

«መሴይ ማንደላይን፤ አሁን እርስዎ የሚጠይቁትን ሥራ ለመፈጸም የሚችል አንድ ሰው ብቻ ነበር የማውቀው::»

ማንደላይን ደነገጠ::

ዣቬር ዓይኑን ከመሴይ ማንደላይን ሳያነሳ የአነጋገሩን ዘይቤ ለወጥ አድርጎ ቀጠለ::

«ይህ ሰው ወንደለኛ ነበር::»

«እሱን ተወው እባክህ» አለ መሴይ ማንደላይን::

«ቱሉን ከተባለ ሥፍራ ታስሮ ነበር::»

የማንደላይን ፊት አመድ መሰለ::

«ወይኔ ተጨፈለቅሁ!» ሲሉ ሽማግሌው ጮኹ::

«ወይኔ ተጨፈለቅሁ!» ሲሉ ሽማግሌው ጮኹ:: ዣቬር አሁንም መሴይ ማንደላይን ቀና ብሎ ተመለከተ:: የተሰበሰበውን ሰው ቃኘ:: የህዝቡ እንዲፈጠጠበት መሆኑን ተገነዘበ:: ከዚያም ቃል ሳይተነፍስ በጉልበቱ ተንበረከከ:: ወዲያው ፈገግታ አሳየ:: ከጋሪው እቃ መጫኛ ስር ከመቅጽበት ገባ::

ሁሉም ተጨነቁ:: ሰው ሁሉ ወሬ ለማየት ተርመሰመሰ:: ለመቀመጫ ይችል እንደሆን ከአንዱም ሁለቴ ሞከረ::

«መሴይ ማንደላይን ከዚያ በቶሎ ብትወጣ ይሻላል» ሲል ሕዝቡ ጮኸ:: ሽማግሌውም ይህንኑ አሉ:: «መሴይ ማንደላይን ከዚያ ቶሎ ብሰ ውጣ:: እኔ ልሙት እንጂ አንተ ምን በወጣህ! ካልወጣህ አንተም ትጨፈለቃለህ::»

ማንደላይን መልስ አልሰጠም:: የተሰበሰበው ሕዝብ እንደገና ዝም አለ:: ጋሪው ሲነካካ ጊዜ የሰሙትን ወደ ውስጥ ይሰምጥ ጀመር:: እንዲያውም ከአካቱው መሴይ ማንደላይን ራሱን ማላቀቅ ተሳነው::

ሰው ተጨነቀ! ግን ጭቃው ውስጥ ሰምጦ የነበረው እግር መነቃነቅ ጀምሮ ቀስ እያለ ወደላይ መጣ:: «ከግራ ቀኝ ያዙ እንጂ» ሲል ማንደላይን ጮኸ:: በአለው ኃይል ለማንሳት ሞከረ:: ሁሉም ለመያዝ የሚችለውን ያህል ያዘ:: የአንድ ሰው ድፍረት ሁሉንም ሰው እንቅንቆ ጉልበት ሰጣቸው:: ሃያ ሰው ያህል ጋሪውን አነሳው:: ሽማግሌው ከሞት ዳኑ::

መሴይ ማንደላይን ተነሳ:: ፊቱ በአንድ ጊዜ የገረጣ መሰለ፤ በኃይል አልቦት ነበር:: ልብሱ በጭቃ ከመለወሱም በላይ አንዳንድ ቦታ ላይ ተቀድዷል:: ሰው ሁሉ አለቀሰ:: ሽማግሌው የማንደላይንን ጉልበት ሳሙ:: «ደጉ አምላክ» ሲሉ ጠሩት:: ራሱም ቢሆን በጣም ደስ አለው:: በእርካታ ዓይን ዣቬርን አየው:: ዣቬር ግን አሁንም በዓይኑ ቁራኛ ይጠብቀዋል::

ደብተራ ፎሽለማ መሳሳጥ እንጂ ስብራት ስላልደረሰባቸው ቶሎ ዳኑ::



ግን ጉልበታቸው አልነቃነቅ ብሎ አስቸገራቸው:: መሴይ ማንደላይን ከሴርቻ ጋር ተነጋግሮ ሽማግሌው ፓሪስ ከተማ አጠገብ ከሚገኝ ገዳም በአትክልተኝነት እንዲሠሩ አስቀጠራቸው::

❀❀❀

## ፱

ፋንቲን ወደ ትውልድ አገርዋ ስትመለስ ከተማው ይህን መስሎ ነው የቆያት:: ማን እንደሆነች ግን ማንም አላስታወሳትም:: ደግነቱ የመሴይ ማንደላይን ፋብሪካ በር ለእርስዋም ተከፍቶ በፈገግታ ተቀበልዋት:: ሴቶች ከሚቀጠሩበት ክፍል ሥራ አግኝታ ሥራ ጀመረች:: ነገር ግን ሥራው ለእርስዋ ጨርሶ እንግዳ ነበር:: የማታውቀው ዓይነት ሥራ ስለነበር ግራ ተጋባች:: ስለዚህ የሚከፈላት ገንዘብ ዝቅተኛ ሆነ:: ግን ትንሽም ቢሆን ለእርስዋ በቂ ነበር:: ሠርታ ለመኖር በመቻልዋ ችግርዋ ተቃለለላት::

ፋንቲን ራስዋን ለማስተዳደር በመቻልዋ በጣም ደስ አላት:: ሰውን ሳያስቸግሩ ራስን ችሎና በሁለት እግር ቆሞ ማደር በጣም ደስ ይላል:: የጉልበትዋን ዋጋ አገኘች:: በመጀመሪያ ወር ደመወዝዋ መስታወት ገዛች:: ውብ የሆነ ሁሩርዋን፤ ከወተት የነጡ ጥርሶችዋን፤ የልጅነት መልክዋን ጠዋት ማታ ለማየት በመቻልዋ ደስታዋ እጥፍ ሆነ:: የሰው ልጅ ራሱን ከማየት የበለጠ የሚያስደስተው ነገር የለም:: ከልጅዋ ከኮዜት በስተቀር ብዙ ነገሮችን ረሳች:: የጠዋት ማታ ሕልምዋ ልጅዋ ነበረች:: ወደፊት ምን ሊሆን እንደሚችል በአሳብ በታያት ጊዜ በደስታ ፈነደቀች:: አንዲት ትንሽ ክፍል ተከራይታ ደመወዝዋን በቅድሚያ በብድር መልክ ወስዳ ክፍልዋን አስጌጠቻት::

«ባል አግብቼ ነበር» ብላ ለመናገር ስለማትችል ስለልጅዋ ሰው ፊት እንዳታነሳ ዘወትር ጥንቃቄ አደረገች:: ሰዎች ይህን ካወቁ «ጋለሞታ» እያሉ ስምዋን ሊያጠፉ እንደሚችሉ ታውቃለች::

ቀደም ሲል እንደተመለከተው ልጅዋን ለወሰዱላት ሰዎች ቃል የገባችበትን ገንዘብ በወር በወር ሳታጓድል ትልክላለች:: ስምዋን ከመፈረም በስተቀር መጻፍ ስለማትችል ለልጅዋ ደብዳቤ ስትጽፍ በሰው ነበር የምታጽፈው::

አዘውትራ ደብዳቤ ትጽፍ እንደነበር ተገንዝበናል:: በመሥሪያ ቤትዋ አካባቢ «ፋንቲን ብዙ ደብዳቤ ትጽፋለች፤ የሚጽፍላትና የምትጽፍለት ሰው

እለ ማለት ነው» ተብሎ ብዙ ተወራ፡፡ ስለዚህ ተከታታይዋ በዛ፡፡ ከዚህም በላይ መልክዋ በተለይ ፀጉርዋና ጥርስዋ በጣም ቆንጆ ስለነበር የሚተናኮሷትም አልጠፉም፡፡

በአማካይ በወር ሁለት ጊዜ ደብዳቤ እንደምትጽፍና ደብዳቤውንም ለተመሳሳይ ሰው እንደምትልክ የሥራ ባልደረቦችዋ ደረሱበት፡፡ ትክክለኛ አድራሻውንም አወቁ፡፡ ደብዳቤ የሚጽፍላት ሽማግሌ መጠጥ ቤት ሲለፈልፍ አግኝተውት በሞቅታ ሁሉንም ነገራቸው፡፡ ፋንቲን ልጅ እንዳላት ተሰማ፡፡

«አንዳንድ ሴቶች አሉ፤ የትም ሲዘሉ ልጅ የሚተፈትፉ፤ የእዚያ ዓይነት ሰው ናት ማለት ነው» እያሉ አሟት፡፡

ፋንቲን ፋብሪካው ውስጥ ሥራ ከጀመረች ወደ ዓመት ገደማ ሆኖአታል፡፡ አንድ ቀን ጠዋት እርስዋ ትሠራበት የነበረው ክፍል ተቆጣጣሪ «ምንድነው?» ብላ ስትጠይቃት አምሳ ፍራንክ በከንቲባው ስም ትሰጣታለች፡፡ የተሰናበተች መሆኑንና ገንዘቡም ለመሰናበቻ ከዚያን እለት ጀምሮ ከሥራ የተሰናበተች መሆኑንና ገንዘቡም ለመሰናበቻ በዘኔታ የሰጣት መሆኑን ትገልጽላታለች፡፡ እንዲረዳት ብሎ ከንቲባው በዘኔታ የሰጣት መሆኑን ትገልጽላታለች፡፡ ከተማውን ለቅቃ ልትሄድ ከንፋ እንደተመታ ዶሮ ክው ብላ ቀረች፡፡ ከተማውን ለቅቃ ልትሄድ አትችልም፡፡ የቤት ኪራይ እዳ አለባት፡፡ አንዳንድ የቤት እቃም በዱቤ ገዝታለች፡፡ ስለዚህ እዳው መክፈል አለባት፡፡ አምሳ ፍራንክ ደግሞ ለዚህ ሁሉ አይበቃም፡፡ ምን እንዳለች ሳታውቅ እንደመጣላት ተናገረች፡፡ ተቆጣጣሪዋ ወደ ቤትዋ እንድትሄድ ምልክት ሰጠቻት፡፡ አፍራና ተክዛ ከሥራዋ ቦታ ወጥታ ወደ ቤትዋ ሄደች፡፡ ጥፋትዋ ምን እንደሆነ በሁሉም ዘንድ ታወቀ፡፡ ለሌሎች ሴቶች አርአያ ልትሆን የምትችል ጋለሞታ! በዚህ ላይ ቅናትም አለ፡፡

መልስ ለመስጠት ኃይል አጣች፡፡ ከንቲባውን እንድታነጋግር ሰዎች መከሩዋት፡፡ ከንቲባው አምሳ ፍራንክ ሰጥቶ አባርሯታል፡፡ ያውም ደግና አዛኝ ሰው ቢሆን ነው እንጂ በገዛ ፋብሪካው ማን ያዝዘዋል፡፡ ያለ ዳረጎት ገዛም ብሎ ሊያባርራትም ይችል ነበር፡፡ «ከዚህ በኋላ ምን ማነጋገር ያስፈልጋል» በማለት ወደ ከንቲባው ሳትሄድ ቀረች፡፡

መሴይ ማንደላይን ስለዚህ ጉዳይ የሚያውቀው ነገር አልነበረም፡፡ ብዙ ጊዜ አዋቂዎች ሥልጣንን ለሚመለከተው ማስተላለፍ እንደ ግዴታ ይቆጥሩታል፡፡ ይህን የመሰለ የሥልጣን ውክልናን መኪት በማድረግ ነበር ተቆጣጣሪዋ ራስዋን ከሳሽ፣ ዳኛና ፍርድ አስፈጻሚ በማድረግ በፋንቲን ላይ የፈረደችውና ከሥራ ያባረረቻት፡፡

ፋንቲን በነበረችበት አካባቢ በግርድና ለመሥራት ሰዎች ይቀጥሯት እንደሆን ከቤት ቤት እየዞረች ጠየቀች፡፡ ማንም ሊቀጥራት አልፈለገም፡፡



ከተማውንም ለቅቃ ለመውጣት አልቻለችም፡፡ የቤት እቃዋን በዱቤ የገዛችው ውራጅ እቃ ከሚሸጡ ባለሱቅ ስለነበር «እዳሽን ሳትከፍዪ ከአገር ብትጠፊ ለፖሊስ ነግሬ ካለሽበት አሲዝሻለሁ» እያሉ ይገዙባታል፡፡ የምትኖርበት ቤት ባለቤት ግን «ወጣት ነሽ፤ ከዚህም በላይ ቆንጆ ስለሆንሽ ያለብሽን የቤት ኪራይ እዳ መክፈል አያቅትሽም» እያሉ ያበረታትዋታል፡፡ አምሳውን ፍራንክ ከፊሉን ቤት ላከራይዋት ስትሰጥ ከፊሉን ለውራጅ እቃ ሻጭ ከፈለች፡፡ የእቃው እዳ ብዙ ስለነበር ለጊዜው በጣም የሚያስፈልጓትን እቃዎች አስቀርታ ቀሪውን ማለት ሦስት አራተኛ የሚሆነውን ለባለቤቱ መለሰች፡፡ የሚቀርባት እዳ ወደ አንድ መቶ ፍራንክ ገደማ ነበር፡፡

ጎረቤትዋ የሆኑ ወታደሮች ልብስ ያሳጥቧት ስለነበር ከዚህ የምታገኘው ገቢ ቆሞ ለመሄድ የሚያስችል ስንቅ መግኘ አደረገቻው፡፡ ለልጅዋ የምትልከው የወር ኪራይ ግን መክፈል አቃታት፡፡

ወደ ትውልድ አገርዋ የተመለሰችለት ያሳደረቻት አሮጊት ተቸግሮ መኖር እንዴት እንደሚቻል የሰጠቻት ትምህርት ለአሁን ኑሮዋ የጨለማ መብራት ሆናት፡፡ ትንሽ ዋሽቶና ትንሽ ገቢ አብቃቅቶ መኖር መቻል የችግር ሁለት ገጽታዎች መሆናቸውን አስረድታት ነበር፡፡ «የመጀመሪያው ስውር ሲሆን ሁለተኛው እንደ ጨለማ ድብቅ ነው» ስትል መክራትም ነበር፡፡

ፋንቲን በጨለማ ያለ መብራት መኖር ለመደችው፡፡ የምትቀምሰውን እራት ለመብላት ከጎረቤት መስኮት በሚመጣ የብርሃን ውጋገን እየተጠቀመች ትጎርሳለች፡፡ እራት ከሌለም ለዓይን ያዝ ሲያደርግ ጥቅልል ብላ መደፋት ነው፡፡

ትምህርት የሰጠቻት አሮጊት ሩህሩህ ሴት ነበረች፡፡ ስምዋ ማርጋሬት ይባላል፡፡ ድሃ ብትሆንም ለተቸገረ አዛኝ፤ ቤተክርስቲያንን መሳም የምታዘወትር ጽኑ አማኝ፤ ምዕዋት መስጠት የሚያስደስታትና ስምዋን ከመፈረም በስተቀር ማንበብና መጻፍ የማትችል ሴት ነበረች፡፡

የሚገርመው፤ ብዙውን ጊዜ እንዲህ ያለው ደግነት፤ እንዲህ ያለው እምነት የኑሮ ደረጃቸው ዝቅተኛ ከሆኑ ሰዎች ዘንድ አይጠፋም፡፡ እንጂ ሲከፋቸው፤ እንደ.ም ደስ ሲላቸው ይኖራሉ፡፡ በነገ በጣም ያምናሉ፡፡ በመጀመሪያ ፋንቲን በጣም አፍራ ለጥቂት ቀናት ከክፍልዋ ሳትወጣ ከቤትዋ ውስጥ ቀጭ አለች፡፡ ከቤት ከወጣች ሰዎች ኋላ ኋላዋ እየተከተሉ ጣት በመቀሰር የሚጠቁሙባት መሰላት፡፡ እውነትም ከቤት በወጣች ቁጥር ሰው ሁሉ ያያታል፤ ሰላምታ ግን አይሰጥዋትም፡፡ መንገደኛ ሁሉ ደግሞ በክፉ ዓይን ሲያያት መጥፎ ስሜት አሳደረባት፡፡ ይህም ስሜት እንደ ጥቅምት ብርድ አካልዋን እየሰረሰረ አስጨነቃት፡፡

ፋንቲን ባዶ እጅዋን የቀረች ደሃ በመሆንዋ ሌሎች እንዲያከብርዋት መጠበቅ የለባትም:: በመጀመሪያ ይህን እውነታ ባትገነዘብም ወደኋላ ኑሮ ስላስተማራት ቀስ በቀስ ደረሰችበት:: ከሦስት ወር በኋላ ምንትዋ-እፍረትዋ ጨርሶ ተገፈፈ:: አደባባይ በደፋ ትወጣ ጀመር:: «ለእኔ እንደሆን ሁሉም ያው ነው» ትላለች ራስዋን በራስዋ ስታናግር:: እንደ አልተሟላላት ኸሬ ብዙ ትለፋለች! ግን የምታገኘው ትንሽ ነው:: በጣም ስለምትለፋ ሰውነትዋ እየዛለ በቀላሉ ለበሽታ በመዳረጉ ሳል ይዞ አጣደፋት:: አንዳንዴ ጎረቤትዋን ማርጋሬትን እየጠራች «እዩ እስቲ ሰውነቴ እንዴት እንደጋለ» ትላለች::

ጠዋት ጠዋት በስባሪ ማበጠሪያ ፀጉርዋን ስታበጥረው ሐር በመሆኑ ደረጃ እያበጀ ስታየው ደስ ይላታል:: ፀጉርዋን አልቆረጠችውም::

ክረምት ሊወጣ ሲል ነበር ከሥራ የተባረረችው:: አሁን የበጋ ወራት ተገባድዶ እንደገና ክረምት ሊገባ ተቃርቦአል:: ክረምት ሲገባ ሁሉም ነገር ጭልምልም ይላል:: ብርድም አጥንት ሰርስር ይገባል:: የሰው ልብም እንደ ብርዱ ይቀዘቅዛል:: ይህ ሁሉ ለፋንቲን ቀላል አልነበረም:: ከዚህም በተጨማሪ ባለእዳዎችም «እዳሽን ክፈዪ እንጂ» እያሉ ጨቀጨቁአት::

ፋንቲን ብዙ ብትለፋም የምታገኘው ገንዘብ በጣም አነስተኛ ስለነበር የነበረባት እዳ እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አልሄደም:: ልጅዋን ያስጠበቀችላት ሰዎች ለረጅም ጊዜ ስላልተከፈላቸው ደብዳቤ እየደጋገሙ ጻፉላት:: የሚያደርሷት ክፉ ቃላት ልብን የሚያቆስሉ ነበሩ:: አንድ ቀን የደረሳት ደብዳቤ ስለልጅዋ ሁኔታ የሚገልጽ ነበር:: «ኮዜት ልብስዋ በሙሉ አልቆ ራቁትዋን ነው ያለችው፤ በአስቸኳይ ቢያንስ አሥር ፍራንክ ላኪና የሚሞቅ የክረምት ልብስ ይግዛላት::»

ደብዳቤውን አንብባ እንደጨረሰች ጭምድድ አድርጋ ከመዳፍዋ ውስጥ አስገብታ ቀኑን ሙሉ ያዘችው:: ወደ ማታ ፀጉር ቤት ሄዳ በምናምን ተጠቅልሎ የነበረውን ፀጉርዋን ለቀቀችው:: ተንዠርግጎ ከኋላዋ ተንከባለለ::

«እንዴ! እንዴት ያለ ፀጉር ነው ያለሽ?» ሲል ፀጉር ሠሪው ጠየቃት::

«ቆርጠህ ብትወስደው ስንት ትከፍለኛለህ?» አለችው::

«አሥር ፍራንክ::»

«ቁረጠው::»

በገንዘቡ ወፈር ያለ ቀሚስ ገዝታ ለልጅዋ ላከችላት:: ባልና ሚስቱ በጣም ተናደዱ:: ገንዘቡን ነበር የፈለጉት:: ቀሚሱን ለራሳቸው ልጅ ለኢፖኒን ሰጥዋት:: ምስኪንዋ ኮዜት የክረምቱን ብርድ የተበጫጨቀ ጨርቅ ብቻ ለብሳ አሳለፈች::



እናት ግን «ልጅ ትንሽ ይሞቃታል፤ በፀጉሬ ሸፈን አለበስኳት» ስትል አሰበች:: የተቆረጠው ፀጉርዋን እንዳይታይ በጨርቅ ሸፈነችው:: ሆኖም አላስጠላባትም:: ነገር ግን ልብዋ ውስጥ መጥፎ ስሜት ማሳደሩ አልቀረም::

ሰው ሁሉ ስላስጠላት ሁሉንም እንደጠላት ማየት ጀመረች:: ለመሲዩ ማንደላይን ብቻ የተለየ ስሜት ነበራት:: ነገር ግን እርሱም ቢሆን ከሥራ ያባረራትና ኑሮዋን ያበላሸባት ስለሆን ለእርሱም የነበራት አክብሮት ከጊዜ በኋላ እየቀዘቀዘ ሄደ:: ሠራተኛ ሲወጣ በአጋጣሚ በፋብሪካው አካባቢ ያለፈች እንደሆን ያበደ ለመምሰል ትስቃለች፤ ትዘፍናለች:: ፋብሪካው ውስጥ የምትሰራ አንዲት ሴት ፋንቲን ስትስቅና ስትዘፍን አይታት «የዚህች ልጅ መጨረሻ አያምርም» ስትል ተነበየች::

ፋንቲን በልጅነትዋ አንድ ወርበላ ወደድኩሽ ብሎ ሲቀርባት ልብዋ ውስጥ ፍቅር ባይኖርም ለጊዜ ማሳለፊያ ብላ አብራው ዘለለች:: ይህ ሰው የማይረባ ዱርዬ ስለነበር በየቀኑ ማታ ማታ ይደበድባታል፤ ይረግጣታል:: በመጨረሻ ልጅ አስታቅፎአት ከአገር ጠፋ:: ጥሎአት በመጥፋቱ በጣም ጠላችው:: ልጅዋን ግን እንደአምላክ ታመልካታለች::

ችግር እየጠናባትና ብቸኝነት በይበልጥ እየተሰማት በሄደ ቁጥር የልጅዋ ፍቅር ግለት እየጨመረ ይሄዳል:: ሰው ሁሉ ሲሸሻት በዓለም ላይ የቀረቻት የእኔ ናት የምትላት ኮዜት ብቻ መሆንዋ ሲታወሳት «ሀብታም ስሆን፤ ሲያልፍልኝ የእኔ ኮዜት ከኔ ጋር ትቀመጣለች፤ አብረን እንኖራለን» ትላለች:: ይህ ሲሆን በአሳብ ሲታያት ፈገግ ትላለች:: ሆኖም በሽታዋ ጠንቶባታል:: ማታ ማታ በጣም እያሳበ ያስላታል::

አንድ ቀን እነሚስተርና ሚስስ ቴናድዬ የጻፉላት ደብዳቤ ደረሳት:: «ሰፈራችን ተስቦ ገብቷል፤ ኮዜትም ታማለች:: የመድኃኒት ዋጋ ደግሞ ንሯል! እየገደለን ነው:: ከአሁን በኋላ መግዣ የለንም:: በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ አርባ ፍራንክ ካላከሽልን ልጅትዋ መሞትዋ ነው» የሚል መልእክት ነበር ደብዳቤው የያዘው::

ክት ብላ ሳቀች:: ወደ ጎረቤትዋ ሄዳ የቁጭት ንግግር ተናገረች::

«ይገርማል!» ጥሩ ሰዎች ናቸው፤ አይደሉም! አርባ ፍራንክ! ያስቡት እስቲ! የቁጃር አጠያየቅ አይደል? ገንዘብ ከየት የሚመጣ ይመስላቸዋል? ደደብ! የቀን ጅቦች አይደሉም!»

ወደ መስኮት ተጠግታ ደብዳቤውን እንደገና አነበበችው:: በደረጃው ወደ ምድር ቤት ወረደች:: ከቤት ወጥታ መንገዱን ተያያዘችው:: ሮጠች! ዘለለች! ክትክት እያለች ሳቀች:: እንደ እብደት አደረጋት::

ከአደባባይ ስትደርስ ብዙ ሰው ተሰብስቦ አየች:: ሰው የተሰበሰበው ከአንድ ጋሪ ዙሪያ ሲሆን ቀይ ልብስ የለበሰ ሰው ጋሪው ላይ ጠጥቶ ይለፈልፋል:: የጥርስ ሐኪም ነበር:: የሐኪሙ ሥራ ከአገር አገር እየዞረ ጥርስ ማከም ስለነበር አሁንም ጥርሱን ያመመው ሰው ካለ እያጠያየቀ ነበር::

ፋንቲን ከሕዝቡ ጋር ተቀላቀለች:: ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ሳቅዋን ለቀቀችው:: የጥርሱ ሐኪም ጥርስ እያወጣ ሳለ ሳቁን ሰምቶ ቀና ሲል ፋንቲንን አያት:: ሐኪሙ በቶሎ ተጣራ:: «አንቺ ከዚያ የምትስቂው! እንዴት ያሉ ጥርሶች ናቸው ያሉሽ? ከወተት የነጡ ናቸው:: እነዚያን የሚያማምሩ ሁለት የፊት ጥርሶችሽን ብትሰጪኝ አርባ ፍራንክ እከፍልሻለሁ» አላት::

«ምንድነው የሚሉት? የፊት ጥርሶችሽ ምንድን ናቸው ነው ያሉት?» ስትል ፋንቲን ጠየቀች::

«የፊት ጥርሶችሽ» አለ ሐኪሙ፤ «የላይኞቹ ማለቴ ነው፤ ብትሸጪልኝ?»

«የሚገርም እኮ ነው» ስትል ፋንቲን ተናገረች::

ጥርሳቸው የወለቀ አሮጊት «አይገርምም! ለጥርስ ነው አርባ ፍራንክ እከፍላለሁ ያለው» አሉ በመገረም:: «ልጅትዋ እድለኛ ናት::»

የሐኪሙን ንግግር ላለመስማት ፋንቲን እየሮጠች ሄደች:: ሐኪሙ ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ:: «ብዙ ገንዘብ ነው የሰጠሁሽ፤ ይጠቅምሻል:: አሳብሽን ከለወጥሽ ወደ ማታ ቲላክ ሆቴል ብቅ በይ፤ ከእዚያ ታገኘኛለሽ::»

ፋንቲን ወደቤትዋ ተመለሰች:: እየሮጠች ነበርና የሄደችው እየቃሰተች የተባለችውን ለወዳጅዋ ለማርጋሬት ነገረቻቸው::

«ምን ልስጥሽ ነው ያለው?» ሲሉ አሮጊትዋ ጠየቁ::

«አርባ ፍራንክ::»

«አርባ ፍራንክ ነው ያልሽው?»

«አዎን አርባ::»

ፋንቲን ይህንኑ እያሰላሰለች ወደ ሥራዋ ሄደች:: ከሩብ ሰዓት በኋላ ሥራዋን አቁማ ደብዳቤውን እንደገና ለማንበብ ወደ መስኮቱ ጠጋ አለች::

ደብዳቤውን አንብባ እንደጨረሰች ወደ ወዳጅዋ ዞር ብላ «ስለተስቦ በሽታ የሚያውቁት ነገር አለ?» ስትል ጠየቀች::



«ያው በሽታ ነዋ ልጄ» ሲሉ መለሱላት::

«ልጆችን ይተናኮላል?»

«በተለይ ልጆችን ይጎዳል::»

«ይገድላል?»

«ብዙ ጊዜ አሉ» ወ/ሮ ማርጋሬት::

ፋንቲን ደብዳቤውን እንደገና ለማንበብ ወደ መስኮት ጠጋ አለች:: ማታ በጊዜ ከቤትዋ ወጥታ ሐኪሙ ወደ ነገራት ሆቴል አመራች::

በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ገና ጎሕ ሳይቀድ ወ/ሮ ማርጋሬት ወደ ፋንቲን ክፍል ሄዱ:: ብዙ ጊዜ አብረው ነበር የሚያመሹት:: በዋዜማው ስላልተገናኙ፣ ሥራም አብረው ስለሆን የሚሄዱት አሮጊትዋ ከፋንቲን ቤት መጡ:: ፋንቲን ከደረቅ የእንጨት ወንበር ላይ ተቀምጣለች:: ፊትዋ ገርጥቷል፤ ዓይንዋ እንባ አቅርሯል:: ሌሊቱን በሙሉ አልተኛችም:: ሻሽዋ ጉልበትዋ ላይ ወድቋል::

ወ/ሮ ማርጋሬት ደነገጡ:: «ምነው? ምን ሆንሽ? ሌሊቱን ቁጭ ብለሽ አደርሽ እንዴ?» ካሉ በኋላ ፋንቲንን አጤንዋት:: ፋንቲን ፊትዋን ቀና አደረገችው:: በአንድ ቀን ከእድሜዋ አሥር ዓመት የጨመረች መሰለች::

«ምንም አልሆንኩም» አለች ፋንቲን:: «እንዲያውም ደስ ነው ያለኝ፤ ልጄ ሳትሞት ነው፤ መንፈሴ ሁሉ የረካ ነው የመሰለኝ::»

ይህን እንደተናገረች ከጥርስዋ ሽያጭ እጅዋ የገባውን አርባ ፍራንክ ለአሮጊትዋ አሳየቻቸው::

«የሥላሴ ያለህ!» አሉ ወ/ሮ ማርጋሬት:: «ይኸ ሁሉ ገንዘብ ከየት ተገኘ? ከሰማይ ነው የወረደው ወይስ ከምድር ፈለቀ?»

«ከየትም ይሁን ብቻ! አግኝቻለሁ» አለች ፋንቲን የኩራት ስሜት አድርባት ፈገግ እያለች:: ሆኖም ፈገግታዋ ዓይንን የሚያሸሽ እንጂ የሚስብ አልነበረም:: ከንፈርዋ በደረቀ ደም ተበክሎአል:: ወሊቀዋም በግልጽ ይታያል:: ሁለቱ የላይኞቹ የፊት ጥርሶችዋ ተነቅለዋል:: ጥርሱ የወጣበት ቀዳዳ በቅጡ አልተደፈነም::

አርባውን ፍራንክ ለልጅዋ አሳዳጊዎች ላከች:: ሚስተርና ሚስስ ቴናድዬ ገንዘብ ለማግኘት የፈጠሩት ዘዴ ነበር እንጂ ኮዜት አልታመመችም::

ፋንቲን ፊትዋን ታይበት የነበረውን መስታወት በመስኮት ወደ ውጭ ወረወረችው::

ባለ እዳዎችዋ በጣም እየጨከኑባት ሄዱ። ያገለገለ እቃ የሚሸጠ ሰውዬ ባገኘዋት ቁጥር «አንቺ እድለቢስ፣ ገንዘቤን አትሰጪኝም?» እያለ ሰደብዋት።

ምን አድርጊ ነው የሚሉዋት? ፋንቲን እንኳን እዳ ልትከፍል ለሆድዋም ስላልሆነላት ከሰውነት ወጥታለች። ልጅዋን የሚያሳድጉላት ባልና ሚስት ሌላ ደብዳቤ ጻፉ።

«ኮዜት ከበሽታዋ ድና በማገገም ላይ ነች። ነገር ግን እስከ ዛሬ የተጠራቀመውን መቶ ፍራንክ አሁኑኑ ካልላክሽ ከቤት አስወጥተን መንገድ ነው የምንጥላት» የሚል ነበር።

«መቶ ፍራንክ! አሁን ደግሞ የት ይሆን ይህን ያህል ገንዘብ የማገኘው? ይሁና!» አለች። «የቀረውን ጥርሴን እሸጣለሁ!»

እድለቢስዋ ፋንቲን የሰው መዘባበቻ ሆነች።

❀❀❀

## ፫

የፋንቲን ታሪክ ምን ዓይነት ታሪክ ነው? ያሽከር ታሪክ! አሽከርን የሚገዛው ሕብረተሰቡ ነው?

ከማን?

ከችግር? ከመከራ? ከስቃይ? ከረሃብ? ከብቸኝነት? የሚቀፍ ግብይ ነፍስ በዳቦ ሲለወጥ! ችግር ግለሰቦች ያልፈቀዱትንና ያልፈለጉትን እንዲሆኑ ሲያስገድዳቸው! ሕብረተሰቡ ደግሞ በግዳጅ የሚያደርጉትን በደስታ ሲቀበል አይገርምም!

ባርነት ቀርቷል ይባላል። ውሸት ነው፤ አልቀረም። አሁንም አለ ግን በአሁኑ ጊዜ ጎልቶ የሚታየው በሴቶች ላይ ነው። ስሙን ቀይረው ዝሙት አዳሪ ይሉታል።

ለ[illegible] የገነው ድራማ ፋንቲን ቀደም ሲል የነበራትን ሁሉ አሟጦ ጨርሶ የቀራት ነገ. [illegible]። ክብርም፣ ስምም፣ እናትነትም፣ ውበትም ምኑ ቅጡ ሁሉም ሄዶአል። ቢሄኒት አካልዋ እንደ በረዶ ቀዝቅዟል ስሜትዋም ሞቷል። የፈለገችውን ነው የምታደርገው። እያወቀች አታውቅም፣ እየሰማች አትሰማም። የተከፋን ፊት አንግታ፣ ሆድ የባሰውን ልብ ተሸክማ፣ እያየ የማያይ ዓይን ሰክታ፣ እየሰማ የማይሰማ ጆሮ



እንዝበልጥላ እንደፈተደችው ትኖራለች። ሕብረተሰብም ሆነ ሕይወት ከፋንቲን ጋር የነበረውን ግንኙነት አቋረጠ። እሷም ለምንም ነገር ደንታ አጣች። ሊደርስባት የሚችል መጥፎ ነገር ሁሉ ደርሶባታል። እርሷም የቻለችውን ያህል ተሸክማዋለች። ሁሉንም አየችው። የነበራትን ሁሉ አጣች። ለሁሉም አለቀሰች፣ አነባች። ታዲያ አሁን ምን ይሆን? ሁሉንም እርግፍ አድርጋ ተወችው። ምቾትና ድሎት ችግርን ስለማያውቁት እንደማይጨነቁለት ሁሉ እንዲሁም ሕፃን ሞት እንቅልፍ መስሎት ዝም እንደሚል ሁሉ እርስዋም ምንም ነገር እንዳልሆነ ቀጥራ ችግር አልተው ቢላት እርስዋ ተወችው። የምትፈራው ወይም የምትሸሸው ነገር የለም። ደመና ቢያጠልልባት፣ ውቅያኖስ ቢደፋባት ምን ደንታ አላት! የኑሮዋ ሰፍነግና ሞልቶ ፈሷል።

የፋንቲን እምነት ይህ ነበር። ግን ተሳስታለች። ማነው እስቲ መጨረሻውን የሚያውቅ? ዛሬ እንዴት እንደሚያልፍ፣ ነገ ደግሞ እንዴት ሆኖ እንደሚመጣ ማን ያውቀዋል? ሁሉንም የሚያውቅ ፈጣሪ አምላክ ብቻ ነው።

ትንንሽ ከተማዎች ውስጥ አሉ አይደል አንዳንድ ልባቸው ያበጠ ጎረምሶች! በትንሽ ገቢ እንደ ሀብታም የሚንቀባረሩ! ጉራቸው አያድርስ፣ ሳይኖራቸው ሀብታም፣ ሳይማሩ ተመራማሪ፣ ያልሆኑትን ለመሆን ሞካሪ፣ ቡና ቤት ሲገቡ የሚጀነኑ፣ ሲጃራ ማጨስ፣ ሸሚዝ መጠቅለል፣ የጫማ ተረከዝ ማስረዘም፣ ሳይነኩ መነጫነጭ፣ «እስቲ ትጂ አባክሽ» ማለት፣ ሻይ ቤት የሚያዘወትሩ፣ አላፊ አግዳሚውን የሚለክፉ፣ ይህን የመሰሉ ሰዎች የትም አሉ። በተለይ ትንንሽ ከተማ ውስጥ እድሜያቸው እየገፋ ሲሄድ እየደደቡ የሚሄዱና በአንጎላቸው ሳይሆን በቂጣቸው የሚያስቡ ሞልተዋል።

በ1823 ዓ.ም. ይህን የመሰለ ጠባይ የነበረው አውደልዳይ፣ ጎፈሬ ብርቱና በመናቂ መስሎ በሰው ስቃይ የሚደሰት ጎረምሳ ነበር። ይህ ጎረምሳ ሰው ከተሰበሰበበት ቡና ቤት ላይ ታች የምትለውን፣ ኑሮ ያንገላታትን፣ የማይሆን ልብስ የለበሰችውና ክቡር ገላዋን ለጎረምሳ አሳልፋ የምትሸጠዋን ሴት ደጋግሞ የሚለክፍ ወጣት ነበር። አንድ ቀን ፋንቲንን እንደልማዱ ለከፋት። እንዳልሰማ ዝም አለችው። ሲጃራ ማጨስ ፋሽን ነውና ተመልሳ በአጠገቡ ስታልፍ የሲጃራ ጭስ አቦነነባት። በአጠገቡ በአለፈች ቁጥር «ፋንጋ፣ እሉቴ፣ የምን መስሳተር ነው? ጥርስ አልጣፋብሽም? እና ሌላም ሌላም እያለ ለደባት። ይህ ሰው ፋንቲንን ሲያናግራት ቀና ብላ እንኳን አላየችውም። ልክ ቅጣት እንደተወሰነበት ወታደር ከወዲያ ወዲህ ንልመጥ ሳትል ወደፊት ትሄድና ትመለሳለች። አሁንም እንደገና ወደፊት ትሄድና ተመልሳ ትመጣለች። ሰውዬው ብዙ ጊዜ ከለከፋት በኋላ በመጨረሻ ዝም

ስትለው በጣም ተናድዶ ኖሮ ቀስ ብሎ ተከትሎአት ይሄድና ልክ ለመመ
ፊትዋን ስታዞር ከመንገድ ግራና ቀኝ ተቆልሎ ከነበረው በረዶ ያን
በጀርባዋ በኩል ይመታታል:: ይህን ጊዜ ልክ እንደነብር ዘልላ አንገቱ ላ
በመጠምጠም በጥፍርዋ ፊቱን ደም በደም አደረገችው:: ሰምቶት የማያው
የስድብ ናዳ አወረደችበት::

ጩኸትዋ በአካባቢው ከነበረው ሻይ ቤት ተሰምቶ ሰዎች ምንድነው ብለው ወጡ:: ቀስ በቀስ ብዙ ሰው ተሰበሰበ:: ሰውዬው አልሞት ባ ተጋዳይ ከሚቧጥጠው ጥፍር ይከላከላል:: የተሰበሰበው ሕዝብ «ብሬ እያለ ይስቃል! ያጨበጭባል:: ፋንቲን መቧጠጥ ብቻ ሳይሆን በጥፊ በርግ ትማታለች::

ድንገት አንድ አረጀም ሰው እየሮጠ መጥቶ ሴትዮዋን በጭ የበካውን ወገብዋን ይዞ «በይ ተከተዪኝ» አላት::

አንገትዋን ቀና አደረገች:: የጋለው ሰውነትዋ በረደ! በቁጣ የነደደው ድምፅዋ ቀዘቀዘ አለ:: በፍርሃት ተንቀጠቀጠች:: የፖሊሱ አዛዥ ዣቬር እንደሆነ አወቀች::

በግርግር አውደልዳዩ ሹልክ ብሎ ከዚያ ጠፋ::

ከዚያ ከብበው የቆሙትን ሁሉ ዣቬር በተናቸው:: ከዚያም ሴትዮዋን እየጐተተ ወደ ቢሮው ወሰዳት:: ቢሮው ከዚያ ሩቅ አልነበረም:: ሴትዮዋ ብዙም ሳታመነታ ተከተለችው:: ቃል አልተነፈሰችም:: ተሰብስቦ የነበረው ሕዝብ ሴትዮዋን ለእብደት በሚዳርግ ፌዝና ሰቆቃ አሸማጠጣት::

ከፖሊስ ጣቢያ እንደደረሱ ዣቬር በር ከፍቶ ፋንቲንን ይዞ ገባ:: በሩን መልሶ ዘጋው:: ፋንቲን እንደ ፈራ ውሻ ቃል ሳታሰማ ጥግ ይዛ ከወለ ላይ ቁጭ አለች:: ዘበኛው መብራት አበራ:: ዣቬር ከኪሱ ወረቀት አውጥ መጻፍ ጀመረ::

የፖሊሱ አዛዥ ከስተርተር ያለ ሰው በመሆኑ ፊቱ ላይ የመቅበጥበ ምልክት አይታይበትም:: ሕግን የማስከበር ጥማቱ የሚያረካበት ቅጽበ በመሆኑ ሥልጣኑን ለማሳየት ተነሳሳ:: የተቀመጠበት ወንበር ትክክ ፍርድ የሚሰጥበት ሥፍራ እንደሆነ ከልቡ ያምናል:: ከሳሽም! ፍር ሰጪም ራሱ ነው:: የሴትዮዋን አድራጎት በደብልጥ በአጤኑ ቁጥር ወንጀ ነትዋን ከመጠራጠር ይገታል:: ወንጀል ስትፈጽም በዓይኑ አይቷል:: አንዲ ሴት አዳሪ አንዱን የከተማ ነዋሪ ከሰው ፊት ደብድባለች:: ለዚህ ጥፋ ዣቬር ራሱ የዓይን ምስክር ነው:: ፀጥ ብሎ ሁኔታውን መዘገበ::

የጊዜውን ሪፖርት መዝግቦ ሲጨርስ ፊርማውን አኖረበት:: ወረቀ



አጣጥፎ ለዘበኛው ሰጠው::

«ሦስት ሰዎች ይዘህ ይህችን ሴት እስር ቤት ውሰድዋት::»

ወደ ፋንቲን ዞር ብሎ «የስድስት ወር እስራት ተፈርዶብሻል» አላት::

እድሉ-ቢስዋ ሴትዮ ሰውነትዋ ተንቀጠቀጠ::

«ስድስት ወር! ወህኒ ቤት ውስጥ ስድስት ወር ሙሉ!» ብላ በኃይል ተነፈሰች:: «ልጄስ!» ስድስት ወር ሙሉ ምን ልትሆን ወይኔ ልጄ! እስከዛሬ ለአንቴናርድዬ ያልከፈልኩት ከመቶ ፍራንክ በላይ እዳ አለብኝ:: ጌታዬ ይህን ያውቃሉ?» ስትል ዣቬርን ጠየቀችው::

መሬት ላይ ተንከባለለች:: ሦስቱ ሰዎች ከአፈሩ ላይ እንደወደቀች ጎትተው አስወጥዋት::

«መሴይ ዣቬር ማሩኝ! ይቅር በሉኝ» ስትል ጮኸች:: «ምንም ዓይነት በደል እንዳልፈጸምኩም! እምልልዎታለሁ:: ከመጀመሪያው ጀምሮ ከሥፍራው ቢኖሩ ኖሮ እውነቱን ያዩ ነበር:: በእግዚአብሔር ስም እምላለሁ! ሰውዬውን አልበደልኩትም:: ያ የማላውቀው ሰውዬ በረዶ አፍሶ ነው የመታኝ:: ዝም ብሎ የሚሄድ መንገደኛን በበረዶ የመምታት መብት አለው? እስቲ ይፍረዱኝ! ያ ነው አውሬ ያደረገኝ:: እንደሚያዩኝ ጤነኛ አይደለሁም:: ሰውዬው 'አንቺ ወሳታ! አንቺ ዱርዬ' እያለ ሰድቦኛል:: ጥርስ እንደሌለኝ አውቃለሁ! ቢሆንም ያስከፋኛል:: ይህ ሆኖብኝ ነው እንጂ ሆን ብዬ ያደረግሁት አይደለም:: እርሱ ዝም ብሎ ነካካኝ እንጂ እኔ አልደረስኩበትም:: ዝም ስለው በረዶ አንስቶ መታኝ:: ጌታዬ መቶ ፍራንክ ያልተከፈለ እዳ አለብኝ:: እዳዬን ካልከፈልኩ ልጄን ከቤታቸው አስወጥተው ሜዳ ነው የሚጥሉብኝ:: ጌታዬ ስለልጄ ብለው ይራሩልኝ:: እኔ ዘንድ እንዳላመጣት አቅም የለኝም:: አዩ ጌታዬ! ከቤታቸው አስወጥተው መንገድ ከጣልዋት ራስዋን ለመጠበቅ የማትችል ሕፃን ናት:: ጊዜው ደግሞ ክረምት ነው:: ለጨቅላዋ ልጄ ይዘኑላት ጌታዬ! በእድሜ ከዚህ ትንሽ ከፍ ያለች ብትሆን እንኳን እንደምንም ብላ ከወዲያ ወዲህ ተሯሩጣ መኖር ትችል ነበር:: በዚህ እድሜዋ ግን አትችልም:: ይራሩልኝ! ይዘኑልኝ ጌታዬ::»

በዚህ ዓይነት ብዙ ለፈለፈች:: ደግማና ደጋግማ መሬት ሳመች:: እጆችዋን ወደ ሰማይ ዘረጋች:: ጉንጮችዋ በእንባ እስኪርሱ ድረስ አለቀሰች! ተንሰቀሰቀች:: እምርሬ እየጮኸች ስታለቅስ ሳልዋ ተነስቶ ደረቅ ሳል ሳለች:: መሪር ጭንቀትዋ ፊትዋ ላይ ጎልቶ ቢታይም የልጅነት ውበትዋን ጨርሶ ሊያከስመው አልቻለም:: ከዚያ የነበሩ ሰዎች አትኩረው ሲመለከትዋት ቆንጆ ሴት ለመሆንዋ አልተጠራጠሩም:: ብድግ ብላ የአዛዡን ኮት ጫፍ ሳመች:: ሁኔታዋ እንደ ድንጋይ የጠጠረ! እንደ በረዶ የቀዘቀዘ ልብን

በቀላሉ የሚያሟሟ ነበር:: ሆኖም እንደ እንጨት የደረቀ ልብን ሊፈ(ታ)
አልቻለም:: ዣቬር አልተበገረም::

«በይ ተነሽ» አለ ዣቬር:: «አትለፍልፊብኝ፤ ይበቃል፤ ም(ን)
ትንፈርቅብኛለች! መንገድሽን ቀጥይ:: ስድስት ወር ተፈርዶብሻል:: ክርስቶስ
እንኳን ይህን ውሳኔ ሊሽር አይችልም::»

በመጨረሻ የተናገረው ቃል እጅግ አስደነገጣት:: «ክርስቶስ እንኳን
ይህን ውሳኔ ሊሽር አይችልም::» መሬት ላይ እንደ ሕፃን ልጅ ተንፈራፈረች::
አሁንም «ማሩኝ» ስትል ጮኸች::

ዣቬር ፊቱን አዞረ:: ፖሊሶቹ ሁለት እጆችዋን ያዙ::

ሴትዮዋ እንደዚያ ስትለፈልፍ ጥቂት ሰዎች ተሰባስበው ነበር:: ከዚያ
በግርግር ማንም
የማይሠራ አንድ ሌላ ሰው ደግሞ ደብቶ ብሎ ቀምሶል:: ... ሰለቆ(መ)
ሳያየው የውጪውን በር ከፍቶ ገብቶ ፊቱን ወደ ግድግዳ አዙሮ
ፋንቲን የተማጠነችውን ሁሉ ሰምቷል::

ፖሊሶቹ እጆችዋን ይዘው ጉትተው ሲያወጥዋት ይህ ሰው ዘወ(ር)
ብሎ «አንድ ጊዜ እስቲ» ሲል አዘዘ:: ፖሊሶቹ እጆችዋን ለቀቁ::

ዣቬር ወጣ ብሎ ሲመለከት ከንቲባው መሴይ ማንደላይን እንደሆ(ነ)
አየ:: ጎንበስ ብሎ እጅ ነሳው:: ሆኖም ፊቱ ላይ የመቆጣትና የመሠየም
ምልክት ይታይበት ነበር::

«ይቅርታ፣ ክቡር ከንቲባ!»

ክቡር ከንቲባ የሚለውን ቃል ስትሰማ የፋንቲን ፊት ተለዋወጠ(ች)
ከመቅጽበት ብድግ ብላ ቆመች:: ሳይታሰብ በድንገት ማንም ሊያቆማት
በማይችል ፍጥነት ተወርውራ ከንቲባው እግር ስር ወደቀች:: ወዲያ(ው)
አንገትዋን ቀና አድርጋና ዓይንዋን አፍጥጣ ከንቲባውን እያየች «የከተማው
ከንቲባ ማለት እርስዎ ነዎት» ካለች በኋላ የፌዝ ሳቅ ሳቀች:: ከዚያ(ም)
ከከንቲባው ፊት ላይ ምራቅዋን ተፋች:: ከንቲባው መሀረቡን አውጥቶ
ፊቱን ከጠራረገ በኋላ የሚከተለውን ተናገረ::

«መሴይ ዣቬር ይህችን ሴት ልቀቅዋትና ትሂድ»

ዣቬር ከመደነቅ ብዛት የሚለውን አጣ:: በጣም ገርሞት አ(ፉ)
እንደከፈተ ቀረ::

ከንቲባው የተናገራቸው ቃላት በዚያው መጠን ፋንቲንንም አፈዘዛት::
ራሱን ያዞረው ሰው እንዳይወድቅ አንድ ነገር ለመያዝ እንደሚጣደፍ (ሁሉ)
እርስዋም እጅዋን ዘርግታ ቶሎ ብላ የደረሰችበትን ቋሚ ያዘች:: ከዚያ(ም)



አካባቢዋን ከቃኘች በኋላ እርስ በራስዋ እንደምትነጋገር ድምፅዋን ዝቅ
አድርጋ ተናገረች::

«ልቀቅዋት! በነፃ ሊለቁኝ! ወህኒ ቤት አልወርድም! ስድስት ወር
አልታሰርም ማለት ነው! ማነው ይህን ያለው? ማንም ይህን ሊል አይችልም፤
ተሳስቼአለሁ:: ይህ ሰው ያ እቡይ ከንቲባ ሊሆን አይችልም:: ወይ መሴይ
ዣቬር ! እርስዎ ኖት፤ ሲያፌዙ ነው 'ልቀቅዋትና ትሂድ' ያሉት አይደለም?
ዣቬር ! እርስዎ ኖት፤ ሲያፌዙ ነው 'ልቀቅዋትና ትሂድ' ያሉት አይደለም?
ቤታቸውን ያከራዩኝን ሰው ሄደው ይጠይቁ:: የቤት ኪራይ በጊዜው
እንደምከፍልና ታማኝ ሰው እንደሆንኩ ራስዎ ሄደው ያረጋግጡ:: እባክዎን
ይቅርታ ያድርጉልኝ፤ ይራሩልኝ::»

ወደ ፖሊሶቹ ዞር ብላ ደግሞ «ይህን ሰው ተመልከቱት፤ እንዴት
እንደተፋሁበት አያችሁ አይደል? የኛ ከንቲባ፣ ሊያስፈራሩኝ አይደለም ከዚህ
የመጡት? እኔ ግን እርስዎን አልፈራም:: እኔ የምፈራው መሴይ ዣቬርን
ብቻ ነው:: ደጉን መሴይ ዣቬርን ብቻ ነው የምፈራው::»

ይህን እንደተናገረች ወደ ከተማው ፖሊስ አዛዥ ፊትዋን አዞረች::

«አይ ጌታዬ! እውነተኛ ዳኛ መሆን አለብዎት:: መሴይ ዣቬር
ትክክለኛ ዳኛ እንደሆኑ አውቃለሁ:: ሴት ልጅን በጠጠረ በረዶ ወርውሮ
መምታት ልክ አይደለም፤ ያውም ሳትደርስበት:: ድብደባውን የተመለከቱት
መኳንንቶች በትርኢቱ ተደስተው ሳቁ:: እኛ ምስኪኖች የእነሱ መደሰቻና
መሳለቂያ ነን:: እርስዎ የደረሱት ከዚያ በኋላ ነው:: እርግጥ ነው እርስዎ
ሕግ የማስከበርና ሥርዓት የማስጠበቅ ኃላፊነት አለብዎት:: ለዚህ ነው
እኔን የያዙኝ:: ግን ነገሩ ትክክል አለመሆኑን ሲረዱ 'ልቀቅዋትና ትሂድ'
አሉ:: ትክክለኛ ዳኛ እንደመሆንዎ አሁንም በድጋሚ ሂጂ ይበሉኝ:: ይህንንም
የሚሉት ለሕፃንዋ ልጄ ሲሉ እንደሆነ አውቃለሁ:: ስድስት ወር ከታሰርኩ
ልጄን ለመርዳትና ለማሳደግ አልችልም:: ሁለተኛ ሌላ ጥፋት አላጠፋም::
እንደፈለጉ ይሳለቁብኝ፤ ይዝለፉኝ፤ መልስ አልሰጣቸውም:: መሴይ ዣቬር
ሁለተኛ ጥፋት አጥፍቼ ከፊትዎ ብቆም እንደፈለጉ ያድርጉኝ፤ እኔም ዝም
እላለሁ:: ዛሬ እኮ ሰውዬው በጣም ስላናደደኝ ነው ዘልዬ ጉብ ያልኩበት::
ደግሞም ነግሬዎታለሁ፤ አሞኛል:: ሳል ይዞ ያጣድፈኛል:: እንዲዚህ ተይዤ
ሳለ በበረዶ ሲመቱኝ ስሜቴ ጋለ፤ ሰውነቴ ተንቀጠቀጠ፤ ራሴን መቆጣጠር
ተሳነኝ:: ሐኪም ደግሞ 'ብትጠነቀቂ ይሻላል' ሲል መክሮኛል:: ቆዩ እስቲ
ጌታዬ እንዲያውም አይፍሩ እንጂ ሰውነቴን ይዳስሱትና ትኩሳቴን ይመልከቱ፤
ይኸውሎት::»

በድንገት የቀሚስዋ መዝጊያ ተፈታና ሳብ ሳብ አድርጋ አስተካከለችው::
ሲጎትትዋት ለካ ቀሚስዋ ተዛንፎ መሸፈን የነበረበት ትከሻዋን ገሃድ

አውጥተውታል። ብድግ ብላ ተነስታ ፖሊሶቹን እጅ በመንሳት ወደ
አመራች።

«ወንድሞቼ፣ የፖሊሱ አዛዥ ትሂድ ብለዋልና መሄዱ ነው» አለ

መሴይ ዣቤር እስከዚያች ደቂቃ ድረስ ቃል ሳይተነፍስ ወደ
እቀርቅሮ ቀርቶ ነበር። ለተመለከተው በታው ተስተካክሎለት እንዲ
ተራውን የሚጠብቅ ሀውልት እንጂ ሰው አይመስልም። ጨርሶ
አላለም።

ሴትዮዋ ራመድ ስትል አንድ ነገር ረግጣ ኖሮ አንሸክሽች። ዣቤ
ይህን ጊዜ ከተዋጠበት የስሜት ባህር ነቅቶ እንገቱን ቀና አደረገ። የተሰ
ሥልጣን ምን እንደሆነ ታሰበው። መቼስ የበታች ሹማምንት ሥል
ሲሰጣቸው እንደ አውሬ ይባላሉ። ትምህርት ወይም የኑሮ ልም
እንዳልሞረደውና በአእምሮ እንዳልበሰለ ሰው ይጩኸናሉ።

«የሃምሳ አለቃ» ሲል ሙኸ። «ይህች አገር በጥባጭና ዱርዬ
መውጣትዋ እንደሆነ አይታይህም? ማነው ትሂድ ብሎ ያዘዘህ?»

«እኔ» አለ ከንቲባው።

ዣቤር የተናገረውን ስትሰማ ሲሰርቅ የተደረሰበት ሌባ የሰረቀው
ቀስ ብሎ እንደሚጥል ሁሉ ፋንቲን የያዘችውን ቀስ ብላ ለቀቀች። የመሴ
ማንደላይንን ድምፅ ስትሰማ ደንግጣ ሌላ ቃል ሳትናገር ፊትዋን አንድ
ወደ ከንቲባው፣ መልሳ ወደ ፖሊሱ አዛዥ እያዞረች ሁለቱን ሰዎ
ማስተያየት ጀመረች። «የትኛው ነው አሁን የተናገረው» ስትል ራስዋ
ጠየቀች። እንኳን መናገር በኃይል መተንፈስ እንኳን አልደፈረችም።

«እኔ» ብሎ መሴይ ማንደላይን ሲናገር የፖሊሱ አዛዥ ዣቤር ፊቱ
ወደ ከንቲባው አዞረ። ፊቱ በንዴት ጠቆረ፣ ደሙ በብስጭት ፈላ፣ ሰው
ተንቀጠቀጠ፤! ድምፁን አክርሮ «ክቡር ከንቲባ፣ ይህ ሊሆን አይችልም
አለ።

«ለምን?» ሲል መሴይ ማንደላይን ጠየቀ።

«ይህች ባለጌ ሴት አንድን የከተማ ነዋሪ ተሳድባለች፣ አስቀይማለች

«ዣቤር» ሲል መሴይ ማንደላይን ረጋ ባለ መንፈስና በዝቅተኛ
ድምፅ መለሰ። «ስማኝ፣ አንተ እውነተኛ ሰው ስለሆንክ ጉዳዩን ባስረዳ
ቅር አይለኝም። እውነቱን ልንገርህ። እንደአጋጣሚ በዚያ ሳልፍ አን
ይህችን ሴት ይዘህ ስትመጣ አይቻለሁ። ብዙ ሰው ስለተሰበሰበ አላየኸኝም
አንተ ከሄድክ በኋላ ስለጉርጉሩ ሰዎችን ጠየቅሁ። ሁሉንም ተረድቼአለሁ
ጥፋተኛው አንተ የምትለው የከተማው ነዋሪ ነው። እርሱን ነበር ፖሊ



መያዝ የነበረባቸው።»

ዣቤር መልስ ሰጠ።

«ይህች ባለጌ ሴት ከንቲባውን ተሳድባለች፣ አስቀይማለች።»

«ይህ እኔን ነው እንጂ አንተን አይመለከትም» አለ መሴይ ማንደላይን።
«ስድቡ የተሰነዘረው በእኔ ላይ ስለሆነ ስለስደቡ እኔው ራሴ የፈለግሁትን
እርምጃ እወስዳለሁ።»

«ይቅርታ ያድርጉልኝ ጌታዬ። ስድቡ የተሰነዘረው በእርስዎ ላይ
ሳይሆን በመንበርዎ ላይ ነው። ይህ ደግሞ መዳኘት አለበት።»

«ዣቤር» አለ ከንቲባው፣ «ትልቁ ዳኛ ሕሊና ነው። ይህች ሴት
የተናገረችውን ሰምቻለሁ። የምሠራውን የማላውቅ አይመስልህ!»

«ክቡር ከንቲባ፣ በእኔ በኩል ደግሞ አሁን የማየውንና የምሰማውን
አላውቅም» አለ የፖሊሱ አዛዥ።

«እንግዲያውስ ትእዛዜን ተቀበል።»

«ግዳጄን ነው የምታዘዘው። ግዳጄ ደግሞ ይህቺ ሴት ስድስት ወር
እስር ቤት መቆየት እንዳለባት ይጠይቃል።»

መሴይ ማንደላይን በእርጋታ የሚቀጥለውን ተናገረ።

«ስማ፣ አንድ ቀን እንኳን አትታሰርም።»

«ክቡር ከንቲባ፣ ቢፈቀድ...»

«ሌላ ቃል አትናገር።»

«ሆኖም...»

«አቁም ብያለሁ» አለ መሴይ ማንደላይን። ዣቤር ቅስሙ ተሰበረ።
እንደ መስኮብ ወታደር ደረቱን ገልብጦ ጥቂት ከቆመ በኋላ ለከንቲባው እጅ
ነስቶ ከቢሮው ወጥቶ ሄደ።

ፋንቲን ወደ በር ሄዳ አየችው። ነገሩ ሁሉ ተመሰቃቀለባት። የሁለቱን
ሰዎች ንግግር በኃፍረት ሰማች። መሴይ ማንደላይን የተናገረው እያንዳንዱ
ቃል ልብዋ ውስጥ የተቀበረውን ጥላቻ እያሟሟ ልብዋን አስከዳት።
የምትሰማውን ማመን አቃታት። በጥላቻው ምትክ ልብዋ በቃላት ሊገለጽ
በማይችል ደስታና ፍቅር ተሞላ።

ዣቤር እንደ ሄደ መሴይ ማንደላይን ፊቱን ወደ ሴትዮዋ አዙሮ
በገርነት እናገራት።

«ያልሽውን ሰምቻለሁ። አንቺ ስላልሻቸው አንዳንድ ነገሮች የማውቀው

ነገር የለም:: ነገር ግን የተናገርሽውን አምናለሁ:: ከተብራከዬ ሥራ ለ
መውጣትሽንም እንኳን አላውቅም ነበር:: ለምን መሞትሽ አላነጋገርሽ
አሁን ግን ያለብሽን እዳ እኔ እከፍልልሻለሁ:: ልጅሽንም አስመጣልሻ
ከፈለግሽ ደግሞ አንቺ ወደ አርስዋ ትሄጃለሽ:: ብትፈልጊ ፓሪስ ወ
ልቦናሽ ከፈቀደው ቦታ መኖር ትችያለሽ:: አንቺንም ሆነ ልጅሽን
እረዳችኋለሁ:: ሥራ መሥራት ካስጠላሽ ከዛሬ ጀምሮ ምንም ሥራ ሳት
ትችያለሽ:: ለመኖር የሚያስፈልጋችሁን ገንዘብ እኔ እሰጣችኋለሁ::
ታማኝነትሽን እንዳታጠፊ:: ከዚህ ሁሉ ይበልጥ ጆሮሽን አቅን
እንድትሰሚኝ የምፈልገው ነገር ቢኖር ከአሁን ቀደም በእግዚአብሔር
ንጽህናሽን ጠብቀሽ እንደኖርሽ ስለማልጠራጠር አሁንም ቢሆን ከዚ
ሰዓት ጀምሮ ከፍትና ምቀኝነት የተለየው ኑሮሽን እንድትቀጥይ አደራ
የምልሽ:: ምስኪኒትዋ፣ አይዞሽ፣ በርቺ::»

ምስኪንዋ ፋንቲን ለመሸከም ከምትችለው በላይ ሆነባት:: ከ
ከዚቤት ጋር አብሮ ለመኖር! ከዚያ አስከፊ ኑሮ መላቀቅ! የገንዘብ ች
ሳይኖር በደስታና በታማኝነት ከዚቤት ጋር መኖር! ይህ ሁሉ ያልታሰበ
ኑሮ ሲታያት እንዴት ትመነው? «ወይኔ፣ ወይኔ» ብሎ ከመሮጥ በስተ
ሌላ ነገር ለማለት አልቻለችም:: ሰውነትዋ ያንን ችሮታ፣ ያንን ደ
ለመሸከም አቅም አነሰው:: ሰውነትዋ ተንዘፈዘፈ:: ከመሲይ ማንደላ
እግር ስር ወደቀች:: ጎንበስ ብሎ ሊያነሳት ሲል እጁን አፈፍ አድር
ሳመችው::

ከዚያም ሕሊናዋን ሳተች::

❀❀❀

# ምሰራፍ አምስት

## ዣቬር

መሲይ ማንደላይን ከቤቱ ውስጥ የሕክምና እርዳታ የሚሰጥ
ክፍል ስለነበረው ፋንቲንን ወደዚያ አስወሰዳት:: የሕክምና እርዳታ የሚሰ
ሴሮች አልጋ ላይ አስተኟዋት:: በኃይል አተኩሳለች:: ሕሊናዋን ሳታው
እንዲሁ እየቃዠች ጥቂት እንደቆየች እንቅልፍ ይዞአት ጭልጥ አለ::

በሚቀጥለው ቀን ወደ ስድስት ሰዓት ገደማ ከእንቅልፍዋ ነ
ከአጠገብዋ ሰው እንደቆመ አየች:: መሲይ ማንደላይን ጣራ ጣራውን



ቆሞአል:: ፊቱ በሀዘኔታ ተሞልቷል:: ከንቲባው ጣራውን ሳይሆን ከግድግዳ ላይ ከፍ ብሎ የተሰቀለውን መስቀል ነበር የሚያየው::

ይህ ሰው መልአክ እንጂ ሰው አይመስላትም:: ሰውነቱ በብርሃን የታነጸ መሰላት:: መሲይ ማንደላይን እየጸለየ ስለነበር ጸሎቱን ላለማቋረጥ ሳትናገር ለረጅም ጊዜ አፍጥጣ አየችው:: በመጨረሻ ግን እየፈራች ቀስ ብላ ተናገረች::

«ምን እየሠሩ ነው?»

መሲይ ማንደላይን ከዚህ ሥፍራ የፋንቲንን መንቃት እየተጠባበቀ ለአንድ ሰዓት ያህል ቆሞአል:: እጅዋን ይዞ የልብዋን አመታት ቆጠረ::

«አሁን ምን ይሰማሻል? ደህና ነሽ!»

«በጣም ደህና ነኝ:: እየበረታሁ ነኝ፤ እንቅልፍ ወሰደኝ» አለች ፋንቲን::

«እንግዲያውስ ወደ ጥያቄሽ ልመለስና ምን ትሠራለህ ስላልሽው ስላንቺው ፈጣሪን በመማጠን ጸሎት እያደረስኩ ነበር::»

ያን እለት ማታ ስለፋንቲን የሕይወት ታሪክ ሲጠይቅ አምሽቶ በሚቀጥለው ቀን ያንኑ ቀጠለ:: ምንም ነገር ሳይቀረው ስለፋንቲን ኑሮ ሁሉንም አወቀ::

«ከመጠን በላይ ስቃይ ተቀብለሻል:: ከአሁን በኋላ ግን ሀዘን አይግባሽ:: በዚህ ዓይነት ነው ሥጋ ለባሾች ወደ መላእክትነት የሚለወጡት:: ከዚህ የተለየ መንገድ እንዳለው አላውቅም:: ይህ አንቺ ያለፍሽበት ምድራዊ ገሀነም ወደ መንግሥት ሰማይ የሚወስድ የመጀመሪያ እርምጃ ነው:: ከዚያ መጀመር ግዴታችን ነው::»

ይህን ካለ በኋላ መሲይ ማንደላይን በኃይል ተነፈሰ:: ፋንቲን ጥቂት ፈገግ ስትል ወላቃ ጥርስዋ ታየ::

መሲይ ማደላይን ወደ እንቴናርድዬ ደብዳቤ ጻፈ:: በደብዳቤው ፋንቲን ያለባት እዳ አንድ መቶ ሃያ ፍራንክ እንደሆነ ገልጾ የላከላቸው ግን ሦስት መቶ ፍራንክ መሆኑን ይጠቅሳል:: በብልጫ ገንዘብ የላከላቸው የፋንቲንን ልጅ ይዘው ወዲያውኑ እንዲያመጡ ነበር:: የልጅትዋ እናት እንደታመመችና ልጅዋን ለማየት እንደጓጓች ገልጾ ነበር ልጅትዋን ይዘው እንዲመጡ የጠየቃቸው::

እንቴናርድዬ ደብዳቤውና ገንዘቡ እንደደረሳቸው በጣም ተደነቁ::

«ሰይጣን» አለ ሚ/ር ቴናርድዬ ለሚስቱ:: «ልጅትዋን አንለቅም:: ምናልባት አንድ ቱል በውብትዋ ተማርኮ ይሆናል ይህን የመሰለ ደብዳቤ

የሚጃፈው።»

ሰውዬው ልጅትዋን በመላክ ፈንታ ሂሣቡን በፖንታቄ አስል[...] ፋንቲን ያለባት እዳ አምስት መቶ ፍራንክ እንደሆነ ገልጾ የመልስ ደብ[...] ለመሴይ ማንደላይን ጻፈለት። ተጨማሪው ሁለት መቶ ፍራንክ ልጅ[...] ቢታመመች ጊዜ ለመድኃኒት የወጣ መሆኑን አስረድቶ ነበር የጻፈው[...]

መሴይ ማንደላይን ደብዳቤው እንደ ደረሰው ሦስት መቶ ፍራ[...] ላከላቸው። ከገንዘቡ ጋር ደግሞ በተቻለ ፍጥነት ክዜትን ይዘው እንዲመ[...] መልዕክት አከለበት።

«በምንም መንገድ ልጅትዋን አንለቅም» አለ ሚ/ር ቴናድዬ።

ፋንቲን በሽታዋ ጠናባት እንጂ ስላልተሻላት አልጋ ላይ ቀ[...] መሴይ ማንደላይን በቀን ሁለት ጊዜ ይጠይቃታል። ሲጠይቃት በ[...] ቁጥር «ክዜትን ቶሎ በዓይኔ የማያት ይመስሉታል?» ስትል ትጠይቀዋ[...]

እርሱም ሲመልስ «ምናልባት ነገ! በማንኛውም ሰዓት ልትደ[...] ትችላለች» ይላታል።

በዚህ ጊዜ የእናተዬዋ የገረጣ ፊት ወገግ ይላል።

«እዬ! እንዴት ደስ ባለኝ!» በማለት ትቆጫለች።

ሕመምዋ እያደር ጠናባት። አንድ ቀን ሐኪሙ የሳምባዋን አተነፋ[...] በማዳመጫ መሣሪያ ካዳመጠ በኋላ ራሱን ነቀነቀ።

«እየተሻላት ነው?» ሲል መሴይ ማንደላይን ጠየቀው።

«ዓይንዋን ለማየት የጓጓችላት ልጅ አላት አይደል!» አለ ዶክተ[...]

«አዎን።»

«እንግዲያውስ ቶሎ ብታስመጡላት ይሻላል።»

መሴይ ማንደላይን በድንጋጤ ሰውነቱ ተንቀጠቀጠ።

«ሐኪሙ ምን አለ?» አለች ፋንቲን።

መሴይ ማንደላይን ፊቱን ፈገግ ለማድረግ ሞከረ።

«ልጅሽን በቶሎ እንድናስመጣልሽና ይህም በሽታሽን ሊያቃል[...] እንደሚችል ነው የነገረን» ካላት በኋላ ወደ ቢሮው ሄደ።

መሴይ ማንደላይን ከቢሮው ውስጥ ቁጭ ብሎ ሥራውን እ[...] ሳለ የፖሊሱ አዛዥ ዣቬር ሊያነጋግረው እንደሚፈልግ ተገለጸለት።

«ይግባ!» አለ።



ዣቬር ገባ።

ለከንቲባው የአክብሮት ሰላምታ ሰጠ። ፊቱን ወደ መስኮት አዙሮ ስለነበር ዣቬር ሲገባ የከንቲባውን ጀርባ ነው ያየው። መሴይ ማንደላይን ቀና ብሎ ሳያየው ወረቀት ማገላበጡን ቀጠለ።

ዣቬር የክፍሉን ፀጥታ ሳያደፈርስ ቀስ ብሎ ወደፊት ተራመደ። ፊቱ ላይ የቆራጥነት ብቻ ሳይሆን የድፍረትም ዓይን በግልጽ ይታያል።

በመጨረሻ ከንቲባው ብዕሩን አስቀምጦ ቀና አለ።

«ታዲያስ፣ ምንድነው ዣቬር? ምን አጋጠመህ?»

ዣቬር አሳቡን ለማሰባሰብ ብሎ ለአጭር ጊዜ ዝም አለ። ከዚያም ድምፁን አለስልሶ ሀዘን በተሞላበት አንደበት «ክቡር ከንቲባ! አንድ ወንጀል ተሠርቷል» አለ።

«የምን ወንጀል?»

«አንድ ግለሰብ አንድን የመንግሥት ባለሥልጣን በስህተት ስለወነጀለ ራሱን ለማጋለጥ ይፈልጋል። እኔ ደግሞ አሁን የመጣሁት ሥራዬ እንደመሆኑ መጠን ይህን ለማሳወቅ ነው።»

«ራሱን ለማጋለጥ የሚፈልገው ሰው ማነው» ሲል መሴይ ማንደላይን ጠየቀው።

«እኔ» አለ ዣቬር።

«አንተ?»

«አዎን፣ እኔ!»

«ማንን በድለህ ነው ራስህን የምታጋልጠው?»

«ክቡርነትዎን።»

መሴይ ማንደላይን ወንበሩን አስተካክሎ ተቀመጠ። ዣቬር ሳይፈራ አሁንም በትህትና ንግግሩን ቀጠለ።

«ክቡር ከንቲባ፣ እኔ አሁን እርስዎን የምጠይቀው ላደረስሁት በደል ከሥራ እንዲያሰናብቱኝና ክስ እንዲመሠርቱብኝ ነው።»

መሴይ ማንደላይን በጣም ተደንቆ ለመናገር አፉን ከፈተ። ዣቬር ቀድሞ ተናገረ።

«ሥራህን ብቻ ልቀቅ ይሉኝ ይሆናል። ግን ይህ ብቻ አይበቃም። በዛ ፈቃድማ ሥራ መልቀቅ መቻል ነበር ነው። ጥፋት ስላጠፋሁና በደል ስለሠራሁ ለፍርድ ቀርቤ መቀጣት አለብኝ። ከሥራም መባረር ይኖርብኛ

ል::»

«እንዴ! በምን ምክንያት?»

«ክቡር ከንቲባ ጉዳዩን ሲያውቁት ይህን ጥያቄ አይጠይቁኝም። ነገሩ ሁሉ ይገባዎታል::»

ዣቬር በኃይል ተነፈሰ:: ሀዘን እየተሰማውና እያፈረ ንግግሩን ቀጠለ:

«ክቡር ከንቲባ ከስድስት ሳምንት በፊት ያቺን ሴት በነፃ ከለቀቋት በኋላ በጣም ተናድጄ ከስሽዎት ነበር::»

«እኔን ነው የከሰስከው?»

«አዎን! ፓሪስ ድረስ ሄጄ ለፖሊስ ጠቅላይ አዛዥ ክሴን አቀረብኩ።»

ብዙ ጊዜ የማይስቀው መሴይ ማንደላይን ከት ብሎ ሳቀ::

«የፖሊስን ሥልጣን ተጋፋ ብለህ ነው የከሰስከኝ?»

«የለም! የጥንት ወንጀለኛ ናቸው ብዬ ነው የከሰስኩዎት::»

ከንቲባው ደንገጥ አለ:: እንዳተረተረ የቀረው ዣቬር ንግግሩን ቀጠለ:

«አልተጠራጠርኩም ነበር:: ለብዙ ጊዜ ጥርጣሬ ነበረኝ:: መልካችሁ ቁመናችሁ፣ ጉልበታችሁ እና ሌላም ሌላም ነገራችሁ ሁሉ ፍጹም አንድ ስለሆነብኝ ዣን ቫልዣ ነዎት ብዬ ደመደምሁ::»

«ማን አልክ? እንዴት ብለህ ነው ስሙን የጠራኸው?»

«ዣን ቫልዣ! ከሃያ ዓመት በፊት የወህኒ ቤት ሹም በነበርኩበት ጊዜ አንድ እስረኛ ነበር:: ይህ ወንጀለኛ ከእስር ቤት ካመለጠ በኋላ የአንድ የተከበሩ ጳጳስ ንብረት ዘርፎአል:: በዚህም አላበቃም! በመሣሪያ ኃይል በማስፈራራት የሌላም ሰው ንብረት ሠርቋል:: ይህን ወንጀለኛ ለመያዝ ብዙ ፍለጋ ቢካሄድም ስምንት ዓመት ሙሉ የት እንዳለ ሳይታወቅ የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ:: ምን አለፋዎት ብቻ ያ ሰው እርስዎ እንደሆኑ ስላመንኩ ለጠቅላይ ፖሊስ አዛዥ ጠቆምኩዎት::»

ዣቬር ንግግሩን ሲያበቃ ወረቀት ማገላበጥ የጀመረው መሴይ ማንደላይን ረጋ ባለ አነጋገር «እና ምን ተባልክ?» ሲል ዣቬርን ጠየቀው::

«አበድክ እንዴ!» አሉኝ::

«ከዚያስ!»

«ከዚያማ እነርሱ ልክ መሆናቸውን አወቅሁ::»

«ጥሩ ገምተሃል::»



«እነርሱ ልክ መሆን አለባቸው:: ምክንያቱም እውነተኛው ዣን ቫልዣ ተገኝቷል::»

መሴይ ማንደላይን የያዘው ወረቀት ከእጁ አምልጦት ወደቀ:: አንገቱን ቀና አድርጎ ዣቬርን አተኩሮ ተመለከተው:: ለስለስ ባለ አንደበት «ተገኘ!» አለው::

ዣቬር ንግግሩን ቀጠለ::

«ክቡር ከንቲባ! ታሪኩ እንዲህ ነው:: ገጠር ውስጥ ሻምፕማትዩ የሚባሉ አንድ የዋህና ደግ ካህን ነበሩ:: እኚህ ካህን በጣም ደሃ ናቸው:: የሚረዳቸው ሰው የላቸውም:: እንደ እርሳቸው ያለ ምስኪን የእለት ተእለት ኑሮ ምን እንደሚመስል ብዙም አይታወቅም:: በመጨረሻ እኚህ የቤተክርስቲያን ሰው ፍሬ ሰርቀው ይያዛሉ:: ፍሬ መስረቃቸው ይህን ያህልም የሚያስወነጅል አልነበረም:: ፍሬ የያዙ ብዛት ያላቸው የፍራፍሬ ዛፎች ተቆርጠው ቅርንጫፎቻቸው በየመንገዱ ይበተናል:: ይህም እንደ ከባድ ጥፋት ተቆጠረ:: ካህኑ የተያዙት ተቀንጥሰው ከወደቁት ቅርንጫፎች አንደኛው ከነፍሬው በእጃቸው ስለተገኘ ነው:: በዚህ የተነሣ ነው ሌባ ተብለው የታሠሩት:: ይህ ጉዳይ ጥቂት ቀን የሚያሳስር እንጂ ብዙ የሚያስፈርድ አልነበረም:: ግን እዚህ ላይ ነው የተፈጥሮ ኃይል ሥራውን የሠራው:: አባታችን ሻምፕማትዩ የታሠሩበት እስር ቤት ስለጠበበ ወደ ሌላ እስር ቤት ይዛወራሉ:: ከአዲሱ እስር ቤት ውስጥ ለብዙ ጊዜ የታሠረ ብሬቬት የሚባል ሌላ እስረኛ ጥሩ ጠባይ በማሳየቱ የእስረኞች ተቆጣጣሪ ሆኖ ይሾማል:: ይህ ሰው ካህኑን ገና ሲያያቸው 'ወንጀለኛውን አገኘሁት! ወንጀለኛውን አገኘሁት' እያለ ይጮሃል::»

«ጌታው ወደዚህ ይመልከቱ! ዣን ቫልዣ አይደሉም?» ሲል ጠየቃቸው::

«ዣን ቫልዣ! ማነው እሱ?» በማለት በመደነቅ ሰውዬውን ለማታለል ይሞክራሉ::

«እንዳላወቀ ለመሆን አይሞክሩ» ይላል ብሬቬት:: «ዣን ቫልዣ ማለት እርስዎ ነዎት:: ከዛሬ ሃያ ዓመት በፊት ቱሉን ከሚገኝ እስር ቤት እስረኛ ነበሩ:: ከእዚያ አብረን ነበርን::»

«አባታችን ሻምፕማትዩ ጨርሰው ካዱ:: ስለጉዳዩ ብዙ ምርመራና ክትትል ተደረገ:: በተደረገው ክትትል የዣን ቫልዣ ቤተሰቦች ከሰላሣ ዓመት በፊት የት እንደነበሩ ተደረሰበት:: ሆኖም ቤተሰቦቹ ያን ጊዜ ከነበሩበት አልተገኙም:: የት እንደሄዱ ደግሞ ማንም ሊጠቁም አልቻለም:: ጊዜው በጣም ስለቆየ ዣን ቫልዣንም ለይቶ የሚያውቅ ሰው ጠፋ:: ሆኖም

ፍለጋው ቀጠለ። ከብሬቬት ሌላ ዣን ቫልዣንን የሚያውቁ ሌሎች ሁለት እስረኞች አሉ። ሁለቱም የእድሜ ልክ እሥራት የተፈረደባቸው ወንጀለኞች ናቸው። ስማቸውም ኮሽፓልና ሼኒልዲዩ ይባላሉ። እስረኞቹ ካሉበት እንዲመጡ ተደርጎ አዩዋቸው። ገና ሲያዩዋቸው ምንም አልተጠራጠሩም። እነርሱም ሆኑ ብሬቬት ሰውዬው ዣን ቫልዣ እንደሆኑ አረጋገጡ። እንደ ዣን ቫልዣ እድሜያቸው 54 ሲሆን ቁመታቸውና መልካቸውም ከዣን ቫልዣ ጋር አንድ ሆኖ ተገኘ። ይህ እውነት ከተደበቀበት የወጣው ልክ እኔ እርስዎ ዣን ቫልዣ እንደሆኑ ክስ በመሠረትኩበት ጊዜ ሲሆን 'አብደሃል ወይ! ዣን ቫልዣ እኮ አራስ ከተባለ እስር ቤት ተገኝቶ አሁን ለፍርድ ሊቀርብ ነው' ሲሉ አባረሩኝ። ምን ያህል እንደደነገጥኩና እንዳፈርኩ ሊገምቱ ይችላሉ። ይህን ዜና እንደሰማሁ ሰውዬውን አምጡና አሳዩኝ ስል ጠየቅሁ። አምጥተው አሳዩኝ።»

«ከዚያስ!» በማለት መሴይ ማንደላይን ጣልቃ ገባ።

ዣቬር ሳይወላወል ሀዘን እየተሰማው ምላሹን ሰጠ።

«ክቡር ከንቲባ፣ እውነት ነው። እውነት ነው። ስለፈጸምኩት ስህተት አዝናለሁ። ሻምፕማትዩ ነኝ ያሉት ሰው በእርግጥ ዣን ቫልዣ ሆነው ነው ያገኟቸው።»

«እርግጠኛ ነህ?»

ዣቬር የፌዝ ሳቅ ሳቀ።

«እርግጠኛ ነህ!» አለ ሰውዬው። «የምትሉት ነገር አይገባኝም። እኔ ሻምፕማትዩ እንጂ ዣን ቫልዣ አይደለሁም አለ»።

«በጣም ሞኝ ሰው ነው። ግን አራት ሰው ስለመሰከረበት ዋሽቶ ሊያመልጥ አይችልም። ተገቢውን ቅጣት ይቀበላል። እኔም የምስክርነት ቃሌን ከሕግ ፊት እንድሰጥ ስለተጠራሁ ወደዚያ እሄዳለሁ።»

መሴይ ማንደላይን ወደ መሬት አቀረቀረ። ብዕር ብሎ ጠረጴዛው ላይ ከነበሩ ወረቀቶች ላይ አፈጠጠ። ሥራ እንደበዛበት ሰው እንዲሁ ይጽፋል፣ ወረቀቶችን ያገላብጣል። ወደ ዣቬር ዞር አለ።

«ይበቃናል ዣቬር! የነገርከኝ ታሪክ ብዙም አላስደሰተኝም። አስቸኳይ የሆኑ ነገሮች ስላሉብኝ ከዚህ ይበልጥ ጊዜ ልናጠፋ! ለመሆኑ ወደ አራስ እስር ቤት መቼ ነው የምትሄደው?»

«ቶሎ ሳልሄድ አልቀርም።»

«ከስንት ቀን በኋላ?»



«ሰውዬው ነገ ለፍርድ ይቀርባል። ስለዚህ ዛሬ ማታ መንገድ እጀምራለሁ ብያለሁ።»

«ቶሎ የፍርድ ውሳኔ የሚሰጥ ይመስልሃል?»

«ሌላ ቀጠሮ የሚሰጥ አይመስለኝም። ግን እኔ የፍርድ ውሳኔ እስኪሰጥ አልጠብቅም። የምስክርነት ቃሌን ሰጥቼ እንደጨረስኩ እመለሳለሁ።»

መሴይ ማንደላይን «መልካም» ካለ በኋላ ዣቬር እጅ በመንሳት አሰናበተው።

ዣቬር ግን ከቢሮው አልወጣም።

«ክቡርነትዎን በድጋሚ ይቅርታ እጠይቃለሁ» አለ ዣቬር።

«ከዚህ በላይ ምን ያስፈልጋል? እኔ እንደሆን ትቼዋለሁ» አለ መሴይ ማንደላይን።

«ክቡር ከንቲባ፣ የጠየቅኩዎትን እንዲያስቡበት።»

«ምንድነው እሱ?»

«ከሥራ እንዲያሰናብቱኝ ነዋ!»

«ዣቬር፣ መከበር ያለብህ ሰው መሆንህን አምናለሁ። ስህተትህን ከሚገባው በላይ አጋነንከው። የተበደልኩት እኔ ስለሆንኩ ይህን ያህል ከቁም ነገር አላስገባሁትም። ከሥራ መባረርን በተመለከተ ከሥራ መባረርህ ቀርቶ እድገት የሚገባህ ስለሆነ በሥራህ ላይ እንድትቆይ ነው የምፈልገው።»

ዣቬር መሴይ ማንደላይንን በጥሞና እየተመለከተ፦

«ክቡር ከንቲባ፣ ይህ ሊሆን አይችልም። በሌላው ሰው ላይ የማደርገው ነገር በእኔም ላይ መፈጸም አለበት። ማንኛውንም የኅብረተሰብ አባልን የበደለ ግለሰብ ያለ ርህራሄ ከአለበት ፈልፍዬ በማውጣት ለፍርድ አቀርባለሁ እያልኩ ለራሴ ዘወትር ቃል ገብቻለሁ። አሁን እኔ ራሴ ሌላውን ሰው በድያለሁና መታለፍ የለብኝም። ስለዚህ ሥራዬን መልቀቅ ይኖርብኛል። እጆች ስላሉኝ የትም ሠርቼ እድራለሁ። ግብርና ብገባም ይሆናል። ለሌሎች ሰዎች ደግሞ ምሳሌ መሆን አለብኝ። ስለዚህ አሁንም ከሥራ እንዲያባርሩኝ በድጋሚ እጠይቃለሁ።»

«እናያለን» ካለ በኋላ መሴይ ማንደላይን ሊጨብጠው እጁን ዘረጋለት።

ዣቬር ከቢሮው ለመውጣት ወደኋላ እያፈገፈገ፦

«ይቅርታ ክቡር ከንቲባ፣ እጅዎን መጨበጥ የለብኝም። አንድ ከንቲባ አንድን ተራ ሰው መጨበጥ የለበትም። ተራ ሰው፣ እያን ተራ ሰው፣ ሥልጣኑን መከታ በማድረግ የሠራውን ሥራ አንድ ተራ ሰላይ ከሚፈጽመው

ተግባር የተለየ አይደለም» ካለ በኋላ ሰጥ ብሎ እጅ ተንስቶ ከቢሮዉ ለመውጣት ወደ በሩ አመራ:: በሩን ከፍቶ ሲወጣም አንገቱን እንደሰበረ ነበር::

«ክቡር ከንቲባ፣ የሥራ ስንብት እስኪተሰጠኝ ድረስ ሥራዬን እቀጥላለሁ::»

በሩን ድሆ ደሀን ከተናገረ በኋላ ወጥቶ ሄደ:: መሲይ ማንደላይን በጣም ተከዞ ቀጭ አለ:: የገርቤርን ውትወታ በመገረም ነበር ያደመጠው::

❀❀❀

# ምዕራፍ ስድስት

# የሻምፕማትዩ ጉዳይ

የታሪኩ አንባቢ እስካሁን በተነገረው መሲይ ማንደላይን ማለት ዣን ቫልዣ እንደሆነ ያውቃል:: ስለዚህ ዣን ቫልዣ ማለት ራሱ እንደሆነ እያወቀ አሁን ሌላ ሰው ዣን ቫልዣ ሆኖ ተገኝቷል ሲሉት ምን ይሰማው ይሆን? ሕሊናው ምን ይላል? ምን ዓይነትስ ፈተና ውስጥ ነው የገባው? ከባሕር ጥልቀትና ከሰማይ ርቀት የላቀው የሰው አእምሮ የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ሲገጥመው ውስጣዊ ስሜቱ ምን ይመስል ይሆን?

እስከዚያን እለት ድረስ ከልቡ ውስጥ ቀብሮ የያዘውን ጉዳይ በድንገት ገርቤር ስላነሳው መሲይ ማንደላይን ከቢሮው ውስጥ ቁጭ እንዳለ መላ ሰውነቱ ራደ:: «መጨረሻዬ ምን ይሆን» ሲል አሰበ:: ውሽንፍር እንደሚያወዛውዘው ቀርካና ከባድ ጦር እንደገጠመው ወታደር ልቡ ከወዲያ ወዲህ ተንከራተተ:: ገርቤር ነገሩን አራገዞም ከቢሮው አልወጣ ብሎት ሲናገር የአገር ደመና ተሰባስቦ ከባድ ዝናብና መብረቅ ከጭንቅላቱ ላይ የሚያዘንብ መሰለው:: ገርቤር እያንጋገረው «ሂድ! ተነሳ! ሩጥ! ሻምፕማቲዩን ነፃ አውጣ! ወደኋላ አትበል! ራስህን አጋልጥ» የሚል ስሜት አደረበት::

«እባ ሻምፕማትዩን ከእስር ቤት አስወጥተህ በእርሳቸው እግር አንተ ተተካ» የሚለው አሳብ ከሕሊናው አልወጣ አለው:: ሆኖም ቀላል ውሳኔ ሲገባ የሚሰማው ዓይነት ስሜት አሳደረበት:: «መጨረሻውን እንያ!» ሲል እርስ በራሱ ተነጋገረ:: በሌላ በኩል «የምን ጀግንነት ነው» ሲል ከራሱ ጋር



ተሟገተ:: በዚህ ዓይነት ሕሊናውና ሥጋው ግብግብ ገጠሙ::

ገና ድሮ ከእስር ቤት እንደወጣ እኚያ ጳጳስ አጥንት የሚሰብር ንግግር ባይናገሩት ኖሮ የዚህ ዓይነቱ ግብግብ ባልገጠመው ነበር:: አንድ ጎኑ «የሚበቃህን ያህል ተሰቃይተሃል! አሁን ራስህን አውጣ» ሲለው ሌላው ጎኑ «እንዴት ባንተ ምክንያት ሌላ ሰው ይጉዳል» እያለ ወተወተው:: ገርቤር ከቢሮው እስከወጣ ድረስ ስሜቱን ለመቆጣጠርና የተገዘናና ለመምሰል ብዙ ታገለ:: ገርቤር እንደወጣ ፋንቲንን ለመጠየቅ ወደ ተኛችበት ክፍል ሄደ:: ከሌላው ቀን ይበልጥ ጊዜ ወስዶ አጫወታት:: ሴሮቹ የተለየ ጥንቃቄ እንዲያደርጉላት በማሳሰብ ምናልባት እራሱ ወደ ተባለ ሥፍራ ሲሄድ እንደሚችል ገለጸላቸው:: ከዚያም ገበታ ቀርቦለት እንክት አድርጎ በላ:: ወደ መኝታ ክፍሉ ገብቶ አሳቡን ሰበሰበ::

ሁኔታውን በአሳብ ሲገመግመው ከዚያ በፊት ተሰምቶ የማይታወቅ ዓይነት ሆነበት:: ድንገት ሳያስበው ከመቀመጫው ብድግ ብሎ የገባበትን ክፍል በር ቆለፈ:: በሩ የተቆለፈ እንደሆነ ማንም ገብቶ ሊያስፈራራው እንደማይችል አመነ:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ የክፍሉን መብራት አጠፋ:: መብራቱ ራሱ አናደደው:: መብራት ከበራ አንድ ሰው ከውጭ ሆኖ ሊያየው እንደሚችል ተገነዘበ::

«ማን? የትኛው ሰው?»

የሚገርመው ግን እንዳያየው የፈለገው ሰው ሁሉ አየው:: የቆለፈው በር ሁሉ ወለል አለ:: ማን ከፈተው? ማን አየው?... ሕሊናው::

ሕሊናው ማለት ሁሉንም የሚያይ አምላክ አየው:: በመጀመሪያ ራሱን ለማታለል ሞከረ:: ከተቆለፈ ቤት ውስጥ ብቻውን ራሱን ከደበቀ ማንም የሚያገኘው አልመሰለውም ነበር:: በሩ ተቆልፎአል! መብራቱ ጠፍቶአል:: ታዲያ ማን ሊያየው ይችላል?

ጭንቅላቱን በሁለት እጆቹ ያዘና ክርኑን ጠረጴዛ ላይ በማስደገፍ ጨለማ ውስጥ ያሰላስል ገባ:: አሳቡን ለማሰባሰብ ቢፈልግም አንጎሉ በቂ ኃይል አጣ:: ሕሊናው ውስጥ የነበረው አሳብ ሁሉ እንደ ማዕበል ተመራጨ:: አሳቡን ለማቆም ይችል ይመስል ጭንቅላቱን በሁለት እጆቹ ጠበቅ አድርጎ ያዘ:: ሆኖም በአሳብ ነጉዶ እንጂ ከተጨበጠ ውሳኔ ላይ ሊደርስ አልቻለም:: ጭንቀቱ እየጉላ ሄደ:: ጭንቅላቱ በእሳት ተያይዞ የሚቃጠል መሰለው:: ወደ መስኮቱ ሄዶ መስኮቱን በኃይል ከፈተው:: ሰማይ ላይ አንዲት ኮከብ እንኳን አትታይም:: ተመልሶ እንደበፊቱ ጭንቅላቱን ይዞ ተቀመጠ:: አንድ ሰዓት አለፈ::

ቀስ በቀስ አሳቡ ተሰብስቦ ወደ አንድ ውሳኔ አመራ:: እኚያ ካህን

የገቡበትን ወጥመድ በጉልህ ለማየት ቻለ፡፡ ከትገርት ኀለም የኑቃ መሰለው፡፡ እኚህ ሰው የእርሱን ጦስ፣ የእርሱን እዳ ተሸክመው በአሳብ እያቸው፡፡ እርሱ መግባት ከነበረበት አዘቅት ውስጥ ሲገቡ ተመለከታቸው፡፡ ከዚያ የመከራ አዘቅት ውስጥ እንዳይገቡ አንድ ነገር መደረግ እንዳለበት አመነ፡፡ ይህን ሊያደርግ የሚችል እርሱ ወይም አንድ ሌላ ሰው መሆን ይኖርበታል፡፡ ግን ከእርሱ ሌላ ማነው ይህን ለመፈጸም የሚችለው?

ነገር ተምታታበት፣ የሚችለው ጉዳይ አልሆነም፡፡ ተጨነቀ፣ ተጠበበ፡፡ እንጎሉ በጭንቀትና በአሳብ ብዛት ሊፈነዳ ሆነ፡፡ ማንም ሰው ቢሆን ከዚያ በፊት ከእንደዚያ ያለ ፈተና ውስጥ የገባ አልመሰለውም፡፡ ሕሊናው አሳደደው፣ እረፍት ነሳው፡፡ «ማሽላ እያረረ ይስቃልና» የፌዝ ሳቅ ሳቀ፡፡ በችኮላ መብራቱን እንደገና አበራው፡፡

«ታዲያ፣ ምን ይጠበስ!» አለ፡፡ «ምን አርበተበተኝ? ምንስ አስጨነቀኝ! እኔ እንደሆን ምንም አልሆንኩም፡፡ ነገሩ ከፍጻሜ ደርሷል፡፡ አንድ ግለሰብ በደል ቢሠራ ጥፋቱ የእኔ አይደል! እኔ እንደሆን ክብር ያለኝ ሰው ነኝ፡፡ ይህ የፈጣሪ ሥራ ነው፡፡ የእርሱ ፈቃድ ይህ ከሆነ እኔ ምን አገባኝ! እርሱ አስተካክሉ የቀየሰውን እኔ ማፍረስ እችላለሁ! ታዲያ ምን ጥልቅ አደረገኝ! አያገባኝም፡፡ በሕይወቴ ዘመን በሕልሜም በውኔም የተመኘሁት ነገር ቢኖር የኑሮ ዋስትና ነበር፡፡ የአምላክ ፈቃድ ሆኖ ያንን አግኝቻለሁ፡፡ ይህን በአምላክ ፈቃድ ያገኘሁትን የኑሮ ዋስትና ማበላሸት የለብኝም፡፡ ታዲያ ለምንድነው የጀመርኩትን እንዳልቀጥል፣ ለሰዎች በጎ ተግባር እንዳልፈጽም፣ ለሌሎች ሰዎች አርአያ እንዳልሆንና የአሳለፍኩት የረጅም ዘመን ስቃይ ውጤት ደስታ እንዳይሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚሆነው? ለማንኛውም ያለቀ ጉዳይ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ሥራ እኔ ልገባ አልችልም፡፡»

ተጨባጭ የሆነ መፍትሔ ሲያጣ ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ክፍሉ ውስጥ ተንቆራጠጠ፡፡ «ና ወዳጄ፣ ከዚህ ይበልጥ ራስህን አታስቃይ» አለ እርሱ በራሱ ሲነጋገር፡፡ ሆኖም የመንፈስ እረፍት ሊያገኝ አልቻለም፡፡ እንዲያውም ከነአካቴው ከመጠን በላይ ተጨነቀ፡፡ የጭንቀቱም ውጤት ብስጭት ሆነ፡፡

ማንም ሰው ቢሆን የባህርን ውሃ ወደ ዳር እንዳይወጣ ለማገድ እንደማይችል ሁሉ አእምሮውም ውስጥ አሳብ እንዳይገባ ለመከልከል አይችልም፡፡ በኃይል እየገፋ የሚመጣውን ውሃ ማዕበል እንለዋለን፡፡ ወንጀል ተሠሪቶ የሚደርሰውን ለቶቃና ጭንቀት ደግሞ የሕሊና ወቀሳ እንለዋለን፡፡ ተፈጥሮ ነፍስንና ውሃን በልዩ ጥበቡ ወደታችና ወደላይ ያንጥራቸዋል፡፡

ጊዜው እያለፈ ሲሄድ እርስ በራሱ መነጋገሩን ቀጥሎ ተናጋሪም



ሰሚም ራሱ ሆነ፡፡ ግን በጣም የሚያስገርመው የሚናገረው ለመስማት የማይፈልገውን ሲሆን ለመናገር አፉን የሚከፍተው ደግሞ ከምንም ጊዜ ይበልጥ ሀጥታ በፈለገበት ወቅት ነበር፡፡

«ይህ ሰው በዚያን ጊዜ የት ነበር? ይሄ ያለቀለት ጉዳይ አይደለም?» ሲል ራሱን ጠየቀ፡፡ ይህን ጥያቄ እንደጠየቀ «እኔን አያገባኝም» ብሎ ማለፍ ስህተት መሆኑን ተገነዘበ፡፡ ንጹህ ሰው ባልሠራው ሥራ ከስቃይ ማጥ ውስጥ ሲወድቅ ገዝም ብሎ ማለፍ ሕሊና ያለው ፍጡር ሊቀበለው የማይችል የአውሬ ጠባይ መሆኑን አመነ፡፡ ይህን እውነታ ለማየት «ራስ-ወዳድ፣ ጨካኝ፣ ፈሪ፣ ወንጀለኛ ያሰኛል» ሲል ወሰነ፡፡

በመጨረሻዎቹ ስምንት ዓመታት የሕይወት ዘመኑ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የደካማ አሳብ መራራነትን ቀመሰ፡፡ ያንን ክፉ አሳብ ከአንጎሉ አውጥቶ ለመጣል ይችል ይመስል እየቀፈፈው ምራቁን ተፋ፡፡

«የሕይወቴ መጨረሻ ምንድነው? ስሜን መደበቅ? ፖሊስን ማታለል? እስከዛሬ የፈጸምኩት በጎ ምግባር መጨረሻው ይሄ ነው? በሕይወቴ ዘመን ውስጥ ከዚህ የተለየ ዓላማ አይኖረኝም ማለት ነው? ነፍሴን ረስቼ ሥጋዬን ብቻ ለማዳን ነው የምጥረው ወይስ የሕይወቴ ግብ ቀና፣ እውነተኛና ታማኝ ሰው ለመሆን ነው? እኚያ ደጉ ጳጳስ ይህ አልነበር ያስደሰታቸው!»

እንደገና ከሕሊናው ጋር ሙግት ገጠመ፡፡ ራሱን ለማውጣት ብሎ የሌላውን ሕይወት ሊያጠፋ እንደሆን ተረዳ፡፡ ታዲያ የዚያን ካህን ሕይወት ካላዳነ ምን ሰው ነው? ይህን ካላደረገ ሰው ሳይሆን አድገቱን ያልጨረሰ አውሬ መሆኑን ተገነዘበ፡፡ ሰው ደግሞ ለራሱ ብቻ ከኖረ መኖር ራሱ ትርጉም አይኖረውም፡፡ እኚያ ጳጳስ ከአጠገቡ ቁጭ ብለው የሚያዩት መሰለው፡፡ በአካባቢው ያሉ ሰዎች የሚያውቁት እንደ ተወዳጅ ከንቲባ ሲሆን ጳጳሱ ግን ከእስር ቤት ያመለጠው ዣን ቫልዣ እንደሆነ ነው የሚያውቁት፡፡ ሰዎች የሚያዩት የውጭ ኑሮውን ሲሆን ጳጳሱ ግን ሕሊናውን ነው የሚያዩት፡፡ እንግዲያውስ ቶሎ ብሎ ወደ አራስ ሄዶ እኚያን ምስኪን ማዳን አለበት፡፡ እውነተኛውን ዣን ቫልዣ አጋልጦ የተሳሳተውን ዣን ቫልዣ ማዳን ይኖርበታል፡፡ ይህን ካደረገ ታላቅ መስዋዕትነትና እስከፊ ድል ይሆናል፡፡ ሆኖም ይህን ከማድረግ ወደኋላ ማለት የለበትም፡፡ እጅግ በጣም አሳዛኝ የሆነ መጨረሻ! በሰዎች ዓይን የሚያስነቅፍ ውሳኔ ሲሆን ይችላል፡፡ በሕሊና ዳኝነት ብቻ ያን ሁሉ ሀብት፣ ያን ሁሉ ደስታ ትቶ ያንን ካህን ለማዳን በገዛ ፈቃድ ራስን አሳልፎ መስጠት!

«ይሁና» አለ፣ «መደረግ ይኖርበታል፣ ይህን ሰው ማዳን አለብኝ፡፡»

እነዚህን ቃላት የተናገራቸው ሳይታወቀው በኃይል እየጮኸ ነበር፡፡

ከጠረጴዛው ላይ የነበሩትን መጻሕፍትና ሌሎች ጽሑፎች በመልክ በመልካቸው አስቀመጠ:: አንዳንዶቹን እሳት ውስጥ ጨመራቸው:: ወረቀት አንስቶ ደብዳቤ ጻፈ:: ደብዳቤውን አሸገው:: አድራሻውን ለአንድ ለታወቀ ባንክ ሥራ አስኪያጅ አደረገው:: ደብዳቤውንና የማስታወሻ ደብተሩን ኪሱ ውስጥ አድርጎ ከወዲያ ወዲህ መንቆራጠጥ ጀመረ::

«ሂድ! ወደኋላ አትበል፤ ራስህን በማጋለጥ ሰውዬውን ካልሠራው ወንጀል አውጣው» የሚለው አሳብ እየጎላበት መጣ:: በሕሊናው ዳኝነት የወደፊት ሕይወቱን የሚወስንበት ሰዓት ተቃረበ:: ከእስር ቤት ከወጣ ወዲህ የአዲስ ሕይወት ምዕራፍ የከፈቱለት እኚያ የሃይማኖት ሰው ነበሩ:: አሁን ደግሞ እኚህ ሽምግምግትዩ የተባሉ የሃይማኖት ሰው የሕይወቱን ሁለተኛ ምዕራፍ ሊከፍቱለት ሆነ:: ከትልቅ ጭንቀት በኋላ የተደረሰበት የውሳኔ ሙግት ነበር::

እኩለ ሌሊት ሆነ:: አሁንም ከወዲያ ወዲህ መንቆራጠጡን ቀጠለ:: ብርድ ብርድ አለው:: እሳት አቀጣጠለ:: መስኮቱቹን መዝጋት እንደነበረበት ዘነጋ:: በመጨረሻ «ራሴን ለማጋለጥና ሰውዬውን ለማዳን ወስኛለሁ» ሲል ሳያውቀው ተናገረ::

በዚህ ጊዜ የፋንቲን ጉዳይ ድንገት ከፊቱ ድቅን አለበት::

«ቆይ እስቲ!» አለ:: «ይህቺ ምስኪን ሴት ደግሞ እንዴት ትሆናለች? እርስዋ ደግሞ ከእዚህ አለች::» ሌላ ችግር ተፈጠረ:: ጨርሶ ያልጠበቀውና ያላሰበው ጉዳይ ነበር::

«እስከዛሬ ለራሴ ብቻ ነበር የምኖረው:: ቢደላኝ፣ ቢከፋኝ፣ ራሴን ላጋልጥ ብል፣ ለነፍሴ ሳይሆን ለሥጋዬ ባድር፣ ያንን ውሳኔ ለማዛባት መንገዴ ላይ የሚቆም ነገር አልነበረም:: ለዚህ ነበር ራሴን እጋልጣለሁ ብዬ የወሰንኩት:: አሁን ግን ይህቺ ሴት አለች:: ለካስ እስከዛሬ ስለሌሎች ሳላስብ ለራሴ ብቻ ነው የኖርኩት? ለካስ ራሴን በጣም ነበር የምወደው? በሰዎች ዓይን ለሌሎች መኖር ታላቅ ክብር የሚያስገኝ ከመሆኑም በላይ ከሥራዎች ሁሉ ክቡር ነው:: እስቲ ነገሩን በንጹህ ልቦና እንየው:: ባለፉት አሥር ዓመታት ከአሥር ሚሊዮን ፍራንክ ይበልጥ ሀብት በማፍራቴና ፋብሪካዎችን በመክፈቴ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ቤተሰቦች በደስታ ሲኖሩ ቻሉ:: በሰበቡ አገሪቱዋም ተጠቅማለች ማለት ይቻላል፤ ምክንያቱም የተወሰኑ ሰዎች ኑሮ በእኔ ምክንያት በመሻሻሉ ውንብድና፣ ዝሙት አዳሪነት፣ ሌብነት፣ ነፍስ የማጥፋት ወንጀልና የመሳሰሉት በተወሰኑ አካባቢዎች ተቀንሰዋል:: እነዚህ ከማጣት ጋር የሚሄዱ ስለመሆናቸው እውን ነው:: ለሌሎች መኖር ማለት ይህ አይደለም? ታዲያ ራሴን የማጋልጠው ይህን ሁሉ ሕዝብ ለማን አደራ



ብዬ ነው! እኔ ከሄድኩ ሥራዬ ሁሉ ተቃወሰ ማለት አይደለም፣ ሥራዬ ከተቃወሰ ደግሞ ሠራተኞቼ ሁሉ የትም መበተኑ ነው:: ለሌሎች መኖር ይኸ የሚሆነው ለዚህ አይደል? ብዙ ቤተሰቦች እንዳይፈቱ፣ ልጆቻቸው የሰው እጅ እንዳያዩ፣ እናቶች በሰቀቀን ማንባታቸው እንዳይደርቅ ብዬ ራሴን ሳላጋልጥ ብቀር ሰዎች በእኔ ላይ ይፈርዱብኝ? ሕሊናዬስ ወደፊት ይገስጸኝ ይሆን? ምን ዓይነት ጣጣ ነው አባቶቼ!»

እንደገና ብድግ ብሎ ከወዲያ ወዲህ መንጎራደድ ጀመረ:: አሁን ግን የሚንጎራደደው እንደ በፊቱ ከጭንቀት ማጥ ውስጥ በመርመጥመጥ ሳይሆን በፈጋ መንፈስ ነበር::

እንቁ ጨለማ ከወረሰውና ጥልቀት ካለው መሬት ውስጥ ተፈልፍሎ እንደሚገኝ ሁሉ እውነትም ከማሰብና ከማሰላሰል ብዛት ይደረስበታል:: ሙሴይ ማንደላይንም ከመጨነቅ፣ ከመጠበብና ከማሰብ ብዛት ከእውነት የደረሰ መሰለው:: ይህም ትክክለኛውን ጎዳና እንዳያይ ጋረደበት::

«አልተሳሳትኩም» አለ ለራሱ፤ «ይኸው ነው ትክክለኛ ጎዳና:: ትክክለኛውን አቅጣጫ ነው የያዝኩት:: ለጭንቀቴ መፍትሔ አገኘሁለት:: ከእዚህ አሳብ ላይ መጽናት አለብኝ:: ምርጫዬ ይኸው ነው፤ ወስኛለሁ:: ከዚህ ወዲያ ስለነገሩ ማውጣትና ማውረድ ወይም መጨነቅ አያስፈልግም:: ይህንንም የምለው ለራሴ በማሰብ ብቻ ሳይሆን ለኅብረተሰቡም በመጨነቅ ጭምር ነው:: እኔ ማንደላይን ስለሆንኩ በማንደላይንነቴ እጸናለሁ:: ይብላኝ ለዣን ቫልዣ! ከአሁን ወዲያ እኔና ዣን ቫልዣ አንድ ሰው አይደለንም:: የዣን ቫልዣን ማንነት አላውቅም:: ዣን ቫልዣ ነው ተብሎ የተጠረጠረው ሰው ራሱን ያውጣ እንጂ እኔ ምን አገባኝ:: አዎን! ከዚህ ውሳኔና መደምደሚያ ላይ በመድረሴ መንፈሴ ረካ:: አሁን ገና የተለየ ሰው መሆኔን ተረዳሁ::»

ጥቂት እንደ መራመድ ብሎ ድንገት ቀጥ ብሎ ቆመ::

«አሬ ወዲያ» አለ:: «ከጥሩ ውሳኔ ላይ ነው የደረስኩት፤ ከዚህች ውሳኔ ንቅንቅ የለም:: ብቻ አሁንም ቢሆንኮ አሳቡ ጨርሶ ከሕሊናዬ ውስጥ ተነቅሎ አልወጣም:: ቢሆንም መወገድ ያለበት ነው:: ከእዚህ ቤት ውስጥ እንደ ምስክር ሆነው ሊናገሩ፣ በአየኋቸው ቁጥር የዚህችን ሰዓት ጭንቀቴን ሊያስታውሱ የሚችሉ ብዙ እቃዎች ስላሉ አሳቤ ብቻ ሳይሆን እነርሱም ጭምር ከዚህ መወገድ አለባቸው::»

ኪሱን ዳብሶ ቦርሳውን ካወጣ በኋላ ከውስጡ አንዲት ትንሽ ቁልፍ አወጣ:: መክፈቻዋ በግድ ከምትታይ የቁልፍ መግቢያ ቀዳዳ ውስጥ ቁልፉን ጨምሮ ሳጥኑን ከፈተው:: ብዙ እቃ አልነበረበትም:: ያረጀ ሱሪ፣ የተበጣጠሰ ጫማ፣ የተቀዳደደ ሸሚዝና እንዲሁም አሮጌ ከረጢት መሳይ ነገርና ያኔ አሁን

ወዳለበት ከተማ ሲገባ ይዞት የነበረው ዱላ ከዚያ ተቀምጦዋል:: መቼ እንዳስቀመጣቸው አስታወሰ::

ወደ በሩ ተመለከተ:: ምንም እንኳን በሩ በሚገባ ተቀርቅሮ ቢዘጋም የሚከፈት መስሎት ፍርሃት ፍርሃት አለው:: ልብሱን፣ ጫማውን፣ ከረጢቱና ዱላው በቅጡ እንኳን ሳይመለከታቸው ቶሎ ብሎ እሳት ውስጥ ጨመራቸው:: እስከዚያን እለት ድረስ በዛብር አስቀምጧቸው ነበር:: በጥቂት ሰከንድ ውስጥ ቤቱ ብርሃን በብርሃን ሆነ:: ሁሉም ጋየ:: ዱላው እየተሰነጣጠቀ ሲነድ የእሳት ብልጭታ ራቅ ወዳለው ሥፍራ ሁሉ ይበትን ጀመር::

ከረጢቱ እየነደደ አንድ የሚያብረቀርቅ ነገር ከአመዱ ውስጥ ታየ:: ጠጋ ብሎ ቢመለከት የብር እቃ መሆኑን ተገነዘበ:: ከእኚያ ጳጳስ ቤት የሠረቀው እቃ ለመሆኑ ታወሰው::

ወደ እሳቱ መመልከቱን ተወ:: እርምጃውን ሳያዛባ ከወዲህ ወዲያ መንቆራጠጡን ቀጠለ:: ወደ እሳቱ ዞር ብሎ ቢያይ እነዚያ ሁለት ከብር የተሠሩ የሻማ ማብሪያዎች መሆናቸውን አረጋገጠ::

«ቆይ እስቲ» በማለት ወደ አሳቡ ተመለሰ:: «ዣን ቫልዣ ማን እንደሆን የሚያስታውሱ ስለሆኑ እነርሱም መጥፋት አለባቸው» ሲል አሰበ:: ነገር ግን እሳቱ ኃይለኛ ስለነበር ሊያቀልጣቸው ካልሆነም ደብዛቸው እስኪጠፋ ሊያበላሻቸው እንደሚችል ስለገመተ የሻማ ማንደጃዎቹን ቀስ ብሎ ከእሳቱ ውስጥ አወጣቸው:: ወደ እሳቱ ጠጋ ሲል ሰውነቱን ትንሽ ስለሞቀው ደስ አለው:: «እንዴት ደስ ይላል» ሲል ተናገረ::

የሻማ ማንደጃዎቹን እያገላበጠ አያቸው:: ለአንድ ደቂቃ ቢቆይ እሳቱ ውስጥ መልሶ ይጨምራቸው ነበር:: ግን ወዲያው ከመቅጽበት «ዣን ቫልዣ፤ ዣን ቫልዣ» ተብሎ የተጠራ መስሎት ጆሮውን አቀና::

ፀጉሩ ቆመ፤ መርዶ የተረዳ መሰለው::

«እምን! ይኸው ነው፤ አልቋል» በማለት ድምፅ ያሰማው ነገር ንግግሩን ቀጠለ:: «የጀመርከውን ብትጨርስ ይሻላል:: የሻማ ማንደጃዎቹንም አቃጥላቸው:: እነርሱም አንተነትህን የሚያስታውሱ ስለሆኑ አጥፋቸው:: እኚያ ጳጳስንም እርሳቸው! ሁሉንም ነገር እርሳ! በሻምፕማትዩ ሕይወት ላይ ፍረድ! እምን ብትፈርድ ይሻልሃል! ብራቮ፣ መልካም ሥራ! ይኸው ነው፣ አልቋል:: ምን አለ! ይህ ሰው ምናልባት ንጹህ ሰው ሊሆን ይችላል:: ብቻ እድሉ ሆነና በአንተ ስም ተጠርጥሮ አዘቅት ውስጥ ሊገባ ነው:: የአንተን ኃጥያት በመሸከሙ ብቻ መጨረሻው የከፋ፣ የስቃይና የመከራ ዘመን ሊያሳልፍ ነው:: ምን አለ! ይሁና! አንተማ ሰዎች በይበልጥ ሊያከብሩህ አንተን ያኑርልን፤ ሺህ ዓመት ከንቲባ ሁነህ ኑር፤ የተጠማን አጠጣ!



የተራበን አብላ፤ እናት አባት የሌለውን ጡር፤ ተባረክ! የሰው ፍቅር ይስጥህ ሊሉህ ነው:: እና አንተ እዚህ ስትደሰት፣ ስትዝዝናና አንድ ሰው ግን የአንተን የጥንት ልብስ ለብሶ፤ ባለማወቅ ስምህን ወርሶ የአንተን የኃጢአት ሰንሰለት እየጎተተ ጨለማ ውስጥ ሊኖር ነው:: ድንቅ፤ ዕጹብ ድንቅ ሥራ! እንዴት ያለው ድርድር ነው! አንተ ርኩስ!»

ፊቱ ላብ በላብ ሆነ:: የሻማ ማንደጃዎቹን በደበዘዘ ዓይኑ ተመለከታቸው:: ከውስጡ የሚወጣው ድምፅ አልተቋረጠም፤ ቀጠለ::

«ዣን ቫልዣ፣ ድምፃቸውን ከፍ እያደረጉ የሚናገሩ ብዙ ድምፆች ይኖራሉ:: ድምፆቹ ለዘላለም ይጮሃሉ! አንተንም ያሞግሳሉ:: ግን ከእነዚህ ድምፆች መካከል አንዱ ብቻ ሌሎች ሳይሰሙት አንተን ያሳድድሃል! በጨለማ ሁሉ ይከተልሃል:: ስማ አንተ ርኩስ! የተረገምክ! ይሄ ሁሉ ሙገሣ፤ ይሄ ሁሉ አክብሮትና አድናቆት ሰማይ ቤት ሳይደርስ ይጠፋል:: ርግማኑ ግን እስከ እግዚአብሔር ፊት ድረስ ይከተልሃል::»

ስውር ሕሊናው ውስጥ በዝግታ የጀመረው ድምፅ ቀስ እያለ እየጎላና ለጆሮው እየቀረበ መጣ:: ያ ድምፅ ንግግሩን ሲጀምር ከራሱ ሕሊና የሚወጣ መሆኑን ቢታወቀውም ከቃላቱ ኃይለኛነት፣ ከድምፁ ጥራትና ጉልህነት የተነሳ እውነትም ከአጠገቡ ሰው ቆሞ የሚገስጸው ስለመሰለው ክፍሉ ውስጥ ሰው እንዳለ ለማረጋገጥ ሲፈራ ሲቸር እየተገላመጠ አየ::

«ማነው?» ሲል ተጣራ:: መጣራቱ ራሱን ስላስገረመው ከት ብሎ የቂል ሳቅ ሳቀ:: «ምን ጅል ነኝ እባካችሁ! ከዚህ ውስጥ ማንም ሊገባ እንደማይችል እያወቅሁ!» ነገር ግን ከክፍሉ ውስጥ አንድ ዓይነት ኃይል ነበር:: ሆኖም ያ ኃይል ለሰዎች ዓይን ጉልህ አልነበረም::

የሻማ ማንደጃዎቹን ከፍ ካለ ሥፍራ ላይ አስቀመጣቸው:: በየተራ የተፈራረቁበትን የተለያዩ ሁለት አሳቦችን አገናዘበ:: ሁለቱም አሳቦች እጅግ የሚያስፈሩ ሆኖ አገኛቸው:: አንዱ ከሌላው አይሻልም:: ሻምፕማቲዩ «ዣን ቫልዣ ናቸው» ተብሎ በጥርጣሬ መያዛቸው ምን ዓይነት አጋጣሚ እንደሆን አስደነቀው:: ስለወደፊት ሕይወቱ እንደገና አሰበ:: ራሱን ያጋልጥ! ግን ስንቱን ሰው ሜዳ ላይ ጥሎ፤ ስንቱን ሰው ወደኋላ ትቶ! ራሱስ ቢሆን ያን ሁሉ ክብሩን፣ ሀብቱ፣ የሰው ፍቅር የምኞት ኑሮና መንደላቀቅን ትቶ እስር ቤት ገብቶ በእግር ብረት ይታሰር! ጨለማ ቤት ይግባ፤ ይልፋ፤ ይሰቃይ፤ ከቀዝቃዛ ሰሚንቶ ላይ ይተኛ:: የእስር ቤት ኑሮ ስቃይ ምን እንደሆነ ለአሥራ ዘጠኝ ዓመት ያየውና ተንገሽግሾ የወጣበት ነው:: የምን ርግማን ነው እባካችሁ! የሕይወት ብሆንም እንደ አዋቂ ተገዝቶና እንደ ሰው ልብ ምቶኛ ይሆናል? ሰው ከእንዲህ ያለ ወጥመድ ውስጥ ገብቶ

መውጫ ያጣል? መንግሥተ ሰማይ ገብቶ ሰይጣን መሆን ወይስ ገሃነም ገብቶ መልአክ መሆን? የፈጣሪ ያለህ! የቱ ይመረጣል? ምንስ ይደረጋል?

ሲቃዩ እንደገና አዲስ ሆኖ አስጨነቀው። ሳፋ ላይ እንደተቀመጠ ውሃ በአሳብ ዋለለ። ተስፋ ሲቆርጡ የሚታየውና በቃላት ለመግለጽ የሚያዳግተው እንዲያው ገም ብሎ ቅርጽ የሚያወጣው የተምታታ ዓይነት ነገር ከፊቱ ድቅን አለ። ከመዳህ ቆሞ መሄድ እንደጀመረ ሕፃን ተንገዳገደ። ጉልህ ሆኖ የሚታየው ነገር አልነበረም፤ ሁሉም ደብዛዛ ሆነበት። ከአንጎሉ የሚወጡ አሳቦች ሁሉ እንደጤስ የተነኑ እንጂ ተሰብስበው ቅርጽ ያላቸው አልሆኑም። ቀኝም ነፈሰ ግራ፣ ግልጽ ሆኖ የታየው ነገር ቢኖር የቀም ሲቃይ መቀበሉን ነበር። በሕይወት እየሉ መሞት! እየተነፈሱ መቀበር!

እንደገና ከጀመረበት ተመለሰ። ይህ ያልታደለ ነፍስ ከአሳብ አሰንጋ ግርፊያ መላቀቅ ስላቃተው በአሳብ መዋተቱን ቀጠለ።

❀❀❀

## ፪

ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ሆነ። አምስት ሰዓት ሙሉ ቂጡ መሬት ሳይነካ ከወዲህ ወዲያ እያለ ቆየ። በዘጠኝ ሰዓት ሰውነቱ ዝሎ ከወንበሩ ላይ አረፍ አለ። ወንበር ላይ እንደተቀመጠ ለካስ እንቅልፍ ወስዶት ኖሮ ይቃዥ ጀመር።

እንደማንኛውም ትዝታ በሕልሙ ያየው ቀደም ሲል ሕሊናውን ስላስጨነቀው ጉዳይ ነበር። ሕልሙ ምንም እንኳን ትዝታ ቢሆንም በይበልጥ እንዲያስብና እንዲጨነቅ አደረገው። ወደ አራስ ከመሄዱ በፊት በእጁ ጽፎ ያስቀመጠውን አሳብ ነበር በሕልሙ ያየው። ምናልባት በወረቀቱ ላይ ተጽፎ የነበረውን አሳብ ቃል በቃል ገልብጠን ብናስቀምጠው ሳይጠቅመን አይቀርም።

የዚህን ሕልም ፍሬ ሀሳብ ሳናከል ብናልፍ ደግሞ በዚያን ሌሊት ምኞት የሆነውን ታሪክ በቁንጽል ማስቀረት ይሆናል። ሕልሙ እንዲት የታመመች ሴት ስለገጠማት ውጣ ውረድ የሚያወሳ ነበር። ታሪኩ እንደሚከተለው ሲሆን በፖስታው ላይ የተጻፈው ቃል «በዚያን ሌሊት ምኞት ያየሁት ሕልም» የሚል ነው።

ከአንድ እርሻ ውስጥ ነበርሁ። የሚያሳገባው ከእርሻ ውስጥ ሳር እንኳን አልበቀለም። ጊዜው ቀን ይሁን ማታ አይታወቅም።



ከወንድሜ ጋር አብረን እንጓዝለን። የልጅነት ወንድሜ ነው። ስለዚህ ወንድሜ ብዙም የማውቀው ነገር የለም። ከነአካቴው መልኩ እንኳን በቅጡ ትዝ አይለኝም። እናወራለን፣ ከእኛ ጋር የሚጓዙ ሌሎች ሰዎች አሉን። ድሮ ስለምናውቃቸውና ዘወትር መስኮት ስለምትከፍት ጎረቤታችን ቤት ነው የምናወራው። እያወራን ሳለ በዚያ በተከፈተ መስኮት በኩል እድርጎ በሚገባ ነፋስ የተነሳ ብርድ ብርድ አለን።

ከእርሻው ቦታ ዛፍ አልነበረም። አንድ ሰው በአጠገባችን ሲያልፍ አየነው። ራቁቱን ነው፤ ምንም ነገር አልለበሰም። ሰውነቱ በጣም ወቋቀርአል። አፈርማ ቀለም ካለው ፈረስ ላይ ተቀምጧል። ሰውዬው መላጣ ሲሆን ከራስ ቅሉ ውስጥ ያሉ የደም ሥሮች በጉልህ ይታያሉ። እንደ ብረት የከበደ ዱላ ይዟል። ምንም ሳይናገር በአጠገባችን አለፈ።

«ጭር ባለው በዚያኛው መንገድ እንሂድ» አለኝ ወንድሜ።

እርሱ ያለውን መንገድ ተከትለን ሄድን። የሚያደናቅፈን እንኳን ዛፍ ቁጥቋጦ አልነበረም። ቀይ አፈር ብቻ ነው የሚታየው። ጥቂት እንደተራመድን ሰምሰጠው እስተያየት መልስ የሚሰጠኝ አጣሁ። ዞር ብል ወንድሜን ከአጠገቤ አጣሁት። በሩቅ ወደሚታይ መንደር አመራሁ። እኚያ ከዚያን የታሠሩበት ከተማ መሰለኝ።

ወደ ከተማው ከሚያስገባው መንገድ ስጠጋ ጭር ማለቱን ተገነዘብኩ። ወደ ሌላ አቅጣጫ አቋርጬ ሄድኩ። ከሁለት መንገዶች መገናኛ አጠገብ አንድ ሰው ግድግዳ ተደግፎ ቆሞአል። «ይህች ከተማ ማን ትባላለች? ስል ጠየቅሁት። ሰውዬው መልስ አልሰጠኝም። የአንድ ቤት በር ሲከፈት ስላየሁ ቤቱ ውስጥ ገባሁ።»

ከፊት ለፊት ከነበረው ክፍል ውስጥ ሰው አልነበረም። ወደሚቀጥለው ክፍል አመራሁ። አንድ ሰው ግድግዳ ይዞ ቆሞአል። «የማን ቤት ነው? እኔስ የት ነው ያለሁት?» ስል ጠየቅሁት። መልስ አልሰጠኝም። ከአጥር ግቢው ውስጥ የአትክልት ቦታ ነበር።

ወደ አትክልቱ ሥፍራ ወጣሁ። ጭር ያለ ሥፍራ ነበር። አንድ ሰው ዛፍ ተደግፎ ቆሞአል። «ይህ ቤት የማነው? እኔስ የት ነው ያለሁት?» ስል ጠየቅሁት። መልስ አልሰጠኝም።

ቶሎ ብዬ ከዚያ ቤት ወጥቼ ሄድኩ። በየመንደሩ ተሿሿርኩ። መንገዱ ሁሉ ጭር ብሏል። የየቤቱ በር ግን ክፍት ነበር። መንገድ ላይ ወፍ እንኳን ዝር አይልም። ድምፅ የሚባል ነገር ፍጹም አይሰማም። ነገር ግን ከየመንገዱ ጥግ፣ ከየቤቱ ግድግዳ ሥር ሰው ቆሞአል። ሆኖም ማንኛቸውም ቢሆኑ ቃል አይናገሩም። የሚደንቀው ደግሞ ማንኛውም ሰው ቢሆን ከቆሙት

ሰዎች መካከል ሁለቱን በአንድ ጊዜ ማየት አይቻልም፤ እነርሱም አይተያዩም። በእያንዳንዱ ሰው አጠገብ ባለፍኩ ቁጥር አተኩሬው ያዩኛል። ከከተማው ወጣሁና ወደ ሜዳው መንገዴን ቀጠልኩ። ጥቂት እንደተጓዝኩ ወደኋላ ዞር ብል ሠራዊት ተከትሉኛል። በየመንገዱና በየጥጉ ሥር ቁመው የነበሩ ሰዎች መሆናቸውን ተገነዘብኩ። የፊት ገጽታቸው የተለየና አስገራሚ ፍጡሮች ናቸው። የተቻኩሉ አይመስሉም፤ ግን ከእኔ ይበልጥ ነበር የሚራመዱት። ሲራመዱ ድምፅ አያሰሙም። በድንገት ሲከቡኝ አየኋቸው። ፊታቸው ቀይ አፈር ይመስላል። ወደ ከተማው ስገባ በመጀመሪያ ያነጋገርኳቸው ሰውዬ 'ወዴት ነው የምትሄደው? ከሞትክ መቆየትህን አላወቅህም እንዴ?' ሲሉ ጠየቁኝ። መልስ ለመስጠት አፌን ስከፍት ከአጠገቤ ሰው አጣሁ»

መሴይ ማንደላይን በጣም በርዶት ከእንቅልፉ ነቃ። ውርጭ ያዘለ ነፋስ ተከፍተው የነበሩትን መስኮቶች ያወዛውዛል። እሳቱ ጠፍቷል። አሁንም እንደጨለመ ስለሆነ አልነጋም። ተነስቶ ወደ መስኮቱ ሄደ። ሰማይ ላይ ከዋክብት አይታዩም። ወደ ውጭ ተመለከተ። አንድ የሚያቃጭል ድምፅ ዓይኑን ሳበው። የጋሪ ኮቴ ነበር የሰማው።

«በዚህ ሰዓት ደግሞ የምን ጋሪ ነው?» ሲል ራሱን ጠየቀ። «ማነው ገና ሳይነጋ በጋሪ የሚሄደው?»

ወዲያው የነበረበት ክፍል በር ሲንኳኳ ሰማ። ከእግር እስከ ራሱ አንድ ነገር ወረረው፤ በጣም ደነገጠ።

«ማነህ?»

አንድ ሰው መልስ ሰጠ።

«ክቡር ክንቲባ፣ እኔ ነኝ።»

አሮጊትዋ የቤት ሠራተኛ እንደሆኑ አወቀ።

«ምነው፤ ምን ፈለጉ?» ሲል ጠየቃቸው።

«ከንጋቱ አሥራ አንድ ሰዓት ሆኖአል ጌታዬ!»

«ታዲያ ምን አለበት!»

«ክቡር ክንቲባ፣ ረሱት እንዴ! ጋሪ በጠዋት እንዲመጣ ብለው አዝዘው ነበር እኮ!»

«ይቅርታ፣ አዎን አዝዤ ነበር።»

አሮጊትዋ ቢያዩት ይደነግጥ ነበር። የሻማ ማንደጃዎቹን ተመለከተ፡ የቀለጠውን ሻማ ጠራረገ። አሮጊትዋ በር ላይ ቆመው ይጠብቃሉ፡



ሲዘገይባቸው «ጌታዬ ባለጋሪውን ምን ልበለው?» ሲሉ እንደገና ጠየቁ።

«ጠብቅ ይበሉት፤ መጣሁ አንድ ደቂቃ!»

ጋሪው አራስ ከተማ ሲደርስ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ይሆናል። እስካሁን ታሪኩን የተከታተልነው ሰው ከጋሪው ወርዶ ወደ ከተማ በእግሩ ተጓዘ።

ከተማውን ከዚያ በፊት አያውቀውም። ለአገሩ ባዳ ለሰዉ እንግዳ ነው። ብዙ ስለተጓዘ ለመመለስ መንገዱ ጠፋው። ከዚያ አካባቢ ፍርድ ቤት እንዳለ እየፈራ አንዱን መንገደኛ ጠየቀው። «ጌታዬ» አለ ሰውዬው፤ «የፍርድ ቤት ሙግት ለመመልከት ፈልገው እንደሆነ ጊዜው መሽቷል። ሥራ የሚያቆሙት በአሥራ ሁለት ሰዓት ነው።»

አደባባይ ካለበት ሲደርሱ ፍርድ ቤቱ ከአንድ ትልቅ ሕንፃ ውስጥ እንደሆነ አመላከተው።

«ጌታዬ እድለኛ ነዎት፤ የፍርድ ቤቱ መብራት አልጠፋም፤ አሁንም ዳኞች ችሎት ላይ ናቸው ማለት ስለሆነ መግባት ከፈለጉ ሊገቡ ይችላሉ። ብርቱ ክርክር ገጥሞዋቸው ይሆናል እስካሁን የቆዩት።»

ወደ ፍርድ ቤቱ አመራ። ቤቱ ጢም ብሎ ሞልቷል። ከጠበቆች አነስተኛ ድምፅ በስተቀር ብዙ ጫጫታ የለም። ፍርድ ቤቱ ቀደም ሲል የሌሎች ሰዎችን ጉዳይ ካየ በኋላ አሁን የሚነጋገረው «ፍራፍሬ ሰርቀዋል» ስለተባለው ስለሻምፐማትዩ ነው። እኚህ ሰው በእርግጥ ፍራፍሬ ለመስረቃቸው ማረጋገጫ አልተገኘም። ማረጋገጫ የተገኘለት ወንጀላቸው ግን ከእስር ቤት መጥፋታቸው ነበር። ምርመራው ቀጥሎ የምስክሮች ቃል ተሰምቷል። አሁን የሚጠበቀው የአቃቤ ሕግ ክርክርና የዳኞች ውሳኔ ነበር። በአዝማሚያው እንደታየው በሰውዬው ላይ እንደሚፈረድ ነበር። ጠበቃቸው ግን በጣም ጎበዝ ሲሆን ከዚያ በፊት በያዘው ጉዳይ ተረትቶ አያውቅም። ሰውዬው ጠበቃ ብቻ ሳይሆን ጥሩ ጸሐፊም ነበር።

የጠባቂዎች ኃላፊ በሩን ከፍቶ ብቅ አለ።

«ጎበዝ እንዴት ነው፤ ልገባ እችላለሁ?»

«አይቻልም» አለ የጠባቂዎች ኃላፊ።

«ምነው?»

«ምክንያቱም ቤቱ ከአፍ እስከ ገደፍ ጢም ብሎ ሞልቶአል»

«ምን ማለትዎ ነው፤ አሁን አንድ መቀመጫ ጠፍቶ ነው?»

«አንድ መቀመጫ! በሩ የተዘጋው ለዚሁ ነው። ከሁን በኋላ ሰው አይገባም።»

የጠባቂዎች ኃላፊ ጥቂት ቆይቶ «እርግጥ ዳኞች ከተሰየሙበት አካ[...] ሁለት ወይም ሦስት ሰው የሚያስቀምጥ ቦታ ነበር! ነገር ግን ከዚያ [...] እንዲቀመጡ የሚፈቀደው ለመንግሥት ባለሥልጣኖች ብቻ ነው::»

ኃላፊው ይህን እንደተናገረ ፊቱን አዞሮ ሄደ:: ይህን ጊዜ ኃላፊው[...] ያነጋገረው ሰዉ ጥቂት አሰበና ከኪሱ ወረቀትና ብዕር አወጣ:: መብራ[...] ወደነበረበት ጠጋ አለ:: «መሴይ ማንደላይን የሞንቴስ ሱር ሞንቴስ ከንቲ[...] ብሎ ከጻፈ በኋላ የጠባቂዎች ኃላፊ ወደሄደበት አቅጣጫ ፈጠን ብ[...] ሕዝቡን አልፎ ሄደ:: ብጣሹን ወረቀት ለጠባቂዎች ኃላፊ ሰጠውና «ይ[...] ወረቀት ለዳኛው ስጣቸው» አለው::

የጠባቂዎች ኃላፊ ጽሑፉን ከተመለከተ በኋላ ለመሀል ዳኛው ወ[...] ሰጣቸው::

የሞንቴስ ሱር ሞንቴስ ከንቲባ ሳይታወቀው ሰው ያከበረውና ያደነቀ[...] መሰለው:: ባለፉት ሰባት ዓመታት ዝናው በሚኖርበት አካባቢ ብቻ ሳይ[...] በመላ ሀገሪቱ ውስጥ ተሰምቶ ነበር:: ቢያንስ እርሱ ከነበረበት ክፍለ ሀ[...] በየአቅጣጫው እስከ ሁለትና ሦስት ክፍለ ሀገሮች ዝናው ዘልቆ ሄዶ ነበ[...]

የሻምፕማቲዩን ጉዳይ የያዙት መሐል ዳኛ ወረቀቱን ሲያዩ ሰውዬው[...] የሚያውቁትና የሚያደንቁት ሰው እንደሆነ አወቁ:: የጠባቂዎች ኃ[...] ወረቀቱን ለዳኛው ሲሰጣቸው ከወረቀቱ በተጨማሪ በቃሉ «እኚህ ሰ[...] የምስክርነት ቃላቸውን ሲሰጡ ይፈልጋሉ» አላቸው:: ወዲያው ዳ[...] ለጠባቂዎች ኃላፊ «አስገባው» ሲሉ ትእዛዝ ሰጡት::

ይህ ታሪኩን የምንከታተለው አሳዛኝና የተከፋ ሰው ወረቀቱን ከሰጠ[...] ሥፍራ አልተንቀሳቀም::

«ጌታዬ ይከተሉኝ» አለው:: ቀደም ሲል ፊቱን ያዞረበት ዘበኛ አ[...] ሰጥ ብሎ እጅ ነስቶ ነው «ይከተሉኝ» ያለው:: የጠባቂዎች ኃላፊ ወዲያ[...] በተራው አንድ ብጣሽ ወረቀት ብጤ ሰጠው:: ጽሑፉም «የመሐል [...] የአክብሮት ሰላምታውን ያቀርባል» የሚል ነበር::

ወረቀቱን ጭምድድ አድርጎ ኪሱ ውስጥ ጨመረው:: ወረቀቱ እ[...] ዓይነት ትዝታ ቀሰቀሰበት:: የጠባቂዎች ኃላፊን ተከትሎ ሄደ:: ወንበ[...] ተከልሎው ከተቀመጠበት ሥፍራ ደረሰ::

«ጌታዬ ይቀመጡ» አለው የጠባቂዎች ኃላፊ:: ሰውዬው እንደሄደ[...] ገድግዳውን ተደግፎ ቆመ! አላበው፤ መተንፈስ አቃተው፤ ሰው[...] ቀጠቀጠ፤ እንደገና ቀጭ አለ:: የተቀመጠበት ቦታ ትንሽ ዞር ያለ ስለ[...] ለሰው በግልጽ አይታይም::



ቀጥሎ እንዳለ አሳቡን የመለወጥ ዝንባሌ ታየበት:: «እስቲ አሁን ማን አስገድዶኝ ነው የመጣሁት» ሲል አሰበ:: ነገር ግን እንዴት እንደሆን ሳይታወቀው ቶሎ ብድግ ብሎ በመራመድ ችሎቱ ውስጥ ዳኞች ከነበሩበት አካባቢ ተጠጋ::

❀❀❀

## ፲

አካባቢው ፣ የሚገባ ታች:: ዳኞች ከፊት ለፊት ከፍ ካለው ምንበር ተቀምጠዋል:: ጠበቆች አፍጥጠዋል:: ጠባቂ ወታደሮች በየጥጉ ተበታትነው ቆመዋል:: የዳኞች ጠረጴዛ በደማቅ ጨርቅ ተሸፍኗል:: የበሮች እጀታ አካባቢ በአድፍ ጠቁረዋል:: «ሰው ሠራሽ ሕግ እውነትን ያወጣል» በሚል እምነት ከዚያ የነበረ ሁሉ በጥሞና ያዳምጣል:: የሰው ብዛት ከመጠን በላይ ስለነበር እርሱን ማንም ልብ አላለውም:: ሰው ሁሉ ይመለከት የነበረው ከወንጀለኞች መቆሚያ ላይ በሁለት ጠባቂዎች ታጅቦ ቆሞ የነበረውን ሰው ነው::

በሁለት ጠባቂዎች ታጅበው የቆሙት ተከሳሹ ሻምፕማቲዩ ነበሩ:: መሴይ ማንደላይን አተኩሮ ተመለከታቸው:: በመልክ መመሳሰላቸውን ተገነዘበ:: በእድሜ ግን ከእርሱ በጣም ያረጁ ይመስላል::

እየቀረበ ሲሄድ የመሐል ዳኛውና አቃቤ ሕጉ በጉልህ ሰላዩትና ስለለዩት በአንገት ሰላም አሉት:: ዳኞቹን፣ ሕግ አስከባሪውንና ከዚያ የነበሩ ጠበቆችና ጠባቂዎች ከሃያ ሰባት ዓመት በፊት ያያቸው መሆኑን አስታወሰ:: አሁንም ከስንት ዓመት በኋላ ከእነዚህ ሰዎች እጅ ሲወድቅ በመሆኑና ውሳኔያቸው ስለአስፈራው ዓይኑን ጨፈነ:: ከፊት ለፊቱ የቆሙት ተከሳሽ «ዣን ቫልዣ ናቸው ተብሎ ነው የተከሰሱት» የሚል አሳብ ስለተሰረጸበትና ሕሊናው እንደ መሳት ስላለ ቶሎ ብሎ ተቀመጠ:: እንደተቀመጠ ዣቬርን በዓይኑ ፈለገው! አላገኘውም:: ሕግ አስከባሪው መንገድ ላይ ስለተቀመጠ ምስክሮችን ሊያያቸው አልቻለም:: ክፍሉም ቢሆን በመጠኑ ጨለምለም ያለ እንጂ በሚገባ ብሎ የበራ ብርሃን አልነበረውም::

ክርክሩ የፈጀው ወደ ሦስት ሰዓት ገደማ ሲሆን ተከሳሹ እንደበተ ርቱዕ ስላልነበሩ የተከሰሱበትን ይክዱ እንጂ በሚገባ አላስረዱም:: እንዲያውም ብዙውን ጊዜ ጣራ ጣራውን ነበር የሚያዩት:: ሲያዩዋቸው ቂላቂልና ጅላጅል ቢጤ ይመስላሉ:: ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በእኚህ ሰው ዝምታ የተነካ ሰው ሁሉ የጠበቀው ከባድ ቅጣት ነው::

ሕግ አስከባሪው የሚከተለውን ተናገረ።

ሕግ አስከባሪው በቅድሚያ ክስ የተረበባቸው በፍራፍሬ ስርቆት ወንጀል «ተከሳሹ በቅድሚያ ክስ የተረበበው ማስረጃ የሠረቁት ፍሬ ከእንቅጠሉ ነበር። ክሱ ሲመሠረት የተረበበው ማስረጃ 'የሠረቁት ፍሬ በእጃቸው ላይ ተገኝቷል' የሚል ነበር። ሆኖም ይህ ብቻ እንደ ማስረጃ ሆኖ ተከሳሹ ከየት እንዳመጡ ለመስረቃቸው ማረጋገጫ ሊሆን አይችልም። ተከሳሹ ከየት እንዳገኙ ተቀጥሮ ለመስረቃቸው ማረጋገጫ ሊሆን አይችልም። እርግጥም የፍራፍሬውን ዥት ሲጠየቁ 'ከመሬት ነው ያነሳሁት' ብለዋል። እርግጥም የፍራፍሬውን ዥት ሲጠየቁ ከመሬት ነው ያነሳሁት ብለዋል። ስለዚህ ፍሬዎችን የያዘ ዛፍ ሊባ ቀጥሮ መንገድ ሊጥለው ይችላል። ስለዚህ ፍሬዎችን የያዘ ዛፍ ሊባ ቀጥሮ መንገድ ሊጥለው ይችላል። ስለዚህ ፍሬዎችን ያስቸግራል። ቅርንጫፍ በመስበር የሰረቁት ሻምፕማንቴዩ ናቸው ለማለት ያስቸግራል። ነገር ግን ከእስር ቤት ይህም በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ሊከሰሱ አይችሉም። ነገር ግን ከእስር ቤት ይህም በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ሊከሰሱ አይችሉም። ምንም እንኳን ያመለጡ ወንጀለኛ ለመሆናቸው በማስረጃ ተረጋግጧል። ምንም እንኳን ያመለጡ ወንጀለኛ ለመሆናቸው ምስክሮች ቢያረጋግጡም ተከሳሹ እስከመጨረሻው ዣን ቫልዣ ለመሆናቸው ምስክሮች ቢያረጋግጡም ተከሳሹ እስከመጨረሻው ክደዋል። ክህደቱን ትተው የፍርድ ቤቱን አስተያየት ቢጠይቁ የሚሻላቸው ክደዋል። ክህደቱን ትተው የፍርድ ቤቱን አስተያየት ቢጠይቁ የሚሻላቸው ለመሆኑ ቢገለጽላቸውም አሻፈረኝ ብለዋል። በተከሳሹ አመለካከት ስለካዱ ለመሆኑ ቢገለጽላቸውም አሻፈረኝ ብለዋል። በተከሳሹ አመለካከት ስለካዱ ከቅጣት የሚያመልጡ መስሎአቸው ይሆናል። በዚህ በኩል ተሳስተዋል። ከቅጣት የሚያመልጡ መስሎአቸው ይሆናል። በዚህ በኩል ተሳስተዋል። ሆኖም ይህ ከእውቀት ማነስ እንጂ ሆን ብሎ የተደረገ ሊሆን አይችልም። ሆኖም ይህ ከእውቀት ማነስ እንጂ ሆን ብሎ የተደረገ ሊሆን አይችልም። ይህም የሆነው ምናልባት ለረጅም ተከሳሹ በእርግጥ ንቃት ይጐድላቸዋል። ይህም የሆነው ምናልባት ለረጅም ጊዜ እስር ቤት ቆይተው በመስቃየታቸው ከዚያም በኋላ ብዙ ስለተንከራተቱ ጊዜ እስር ቤት ቆይተው በመስቃየታቸው ከዚያም በኋላ ብዙ ስለተንከራተቱ ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ በሌላም፣ በሌላም ምክንያት ሊሆን ይችላል። ሆነም ቀረም የእርሳቸው አነጋገር አለማወቅ ወይም ችሎታ ማነስ ከሚሰጠው ሆነም ቀረም የእርሳቸው አነጋገር አለማወቅ ወይም ችሎታ ማነስ ከሚሰጠው ብያኔ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር አይገባም። ነገር ግን ተከሳሹ ዣን ቫልዣ ብያኔ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር አይገባም። ነገር ግን ተከሳሹ ዣን ቫልዣ እንደሆኑና የቅጣት ዘመናቸውን ሳይጨርሱ አምልጠው ለመጥፋታቸው እንደሆኑና የቅጣት ዘመናቸውን ሳይጨርሱ አምልጠው ለመጥፋታቸው ጥርጥር የለውም። ስለዚህ ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆነው በመገኘታቸው በወንጀለኛ ጥርጥር የለውም። ስለዚህ ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆነው በመገኘታቸው በወንጀለኛ መቅጫ አንቀጽ... መሠረት ተገቢውን ቅጣት ይቀበላሉ።»

ሕግ አስከባሪው ዳኞች ስለሰጡት አስተያየትና ስለፈጸሙት ጥልቅ ምርምር በቅድሚያ ምስጋናውን አቅርቦአል። ተከሳሹን ግን የዳኞቹን ትንተና መሠረት በማድረግ በጣም ነቅፎዋቸዋል። ተከሳሽ ዣን ቫልዣ እንደሆኑ ስለመረጋገጡ ሲያስረዳ «ዝም ማለታቸው ነገሩን አምነው እንደተቀበሉ ያሳያል» አለ። «ቀደም ሲል ግን ክደው ነበር። ለመሆኑ ዣን ቫልዣ ማነው? ዣን ቫልዣ የተተፋ! አገር የጠላውና ሊላም ሊላም ሰው ነው።»

ሕግ አስከባሪው ይህን ሲናገር ከዚያ የነበረ ሰው ሰውነት ሁሉ ስቅጥጥ አለ። «ሻምፕማንቲዩ ማለት ዣን ቫልዣ ነው» ተብሎ ክስ ሲመሠረት «ዦርናል ደ ላ ፕሪፌትየር» የተባለ ጋዜጣ ዣን ቫልዣ ማን እንደሆነ ሲያስረዳ «ዣን ቫልዣ ማለት ወሮበላ! ለማኝ፣ ቀጣፊ፣ መተዳደሪያ የሌለው አውደልዳይ፣ ሕይወቱን ወንጀል በመሥራት የሚመራ እንዲሁም ሊላም ሊላም ቅጽል ሊሰጠው የሚገባ ነው» ብሎ እንደጻፈ ተናገረ።



«ይህ ሰው ፍራፍሬ ሠርቆ ቢያዝም አድራጐቱን ክዷል። እንዲሁም ከእስር ቤት ለማምለጡም ከሕግ ፊት ክዷል። የሚገርመው የገዛ ስሙን እንኳን የካደ ሰው ነው። ምን ያልካደው ነገር አለ! ሕልውናውን ጨምሮ ነው የካደው ለማለት ይቻላል። ነገር ግን እርሱ ሽንጡን ገትሮ ቢክድም አራት ምስክሮች መስክረውበታል። የተከበሩትና ውሸት የማያውቁት የፖሊስ አዛዥ ዣቬር እንኳን በእርሱ ላይ መስክረዋል። እስር ቤት ውስጥ ከተከሳሹ ጋር አብረው ታስረው ከነበሩት ሰዎች መካከል ሦስት እስረኞችም መስክረውበታል። እነዚህ ምስክሮች ከመሰከሩበት በኋላ እንኳን ወንጀሉን አምኖ ይቅርታ አልጠየቀም። ስለዚህ ማኅበራዊ ኑሮን ሊያፋልስ ታጥቆ የተነሣ ወንጀለኛ ስለሆነ ቅጣቱ ሊቀልለት አይገባም።»

ሕግ አስከባሪው ይህን ማብራሪያ ሲሰጥ ካሁኑ ተከሳሽ አፋቸውን ከፍተው በመገረምና በመደነቅ አዳመጡ። ሕግ አስከባሪው አንደበተ ርቱዕ በመሆኑ ቢያደንቁትም በማያውቁት ነገር እንደዚያ ስለወረደባቸው ከልብ ረገሙት። ግራ ቀኙን ከቃኙ በኋላ ተከሳሹ ራሳቸውን ነቀነቁ።

ሕግ አስከባሪው ትችቱን በመቀጠል «ማንም ሰው ወንጀል ሊሠራ ወይም ውሸት ሊናገር ይችላል። ግን ከሕግ ሊያመልጥ አይችልም። ይህ ሰው ግን ወንጀል ከመፈጸም አልፎ ከሕግ ለማምለጥ ሞክሮአል። ይህም ከባድ ወንጀል በመሆኑ በእድሜ ልክ እስራት እንዲቀጣ አሳብ አቀርባለሁ።»

«ስለተሰጠው አስተያየት የምትሰጠው መልስ አለ?» ሲሉ ዳኛው ተከሳሹን ጠየቋቸው። ቆባቸውን ያፍተለትሉ የነበሩት ተከሳሽ ምንም ነገር እንዳልሰማ ዝም አሉ።

ዳኛው ጥያቄውን ደገሙላቸው።

አሁን ግን ጥያቄውን ስለሰሙ ዳኛው ምን ማለት እንደፈለጉ ገባቸው። ከእንቅልፍ እንደነቃ ሰው ከወዲያ ወዲህ ተመለከቱ። ዳኞቹን፣ ሕግ አስከባሪውን፣ ጠበቆቹንና ተመልካቹን ሕዝብ አፍጥጠው ካዩ በኋላ ከፊት ለፊት የነበረውን መከለያ ብረት አጥብቀው ይዘው በድንገት በከፍተኛ ድምፅ መናገር ጀመሩ። ቃላት ተሸቀዳድመው «እኔ ልቅደም፣ የለም እኔ ልቅደም» ያልዋቸው ይመስል እየተቻኮሉ በጣም በፍጥነት ተናገሩ።

«የምለውን በጥሞና አድምጡኝ። ከመሴይ ባሉፐ ሱቅ ውስጥ ሲጋሪ የሚሆን የብረት ተሽከርካሪ ሠራተኛ ነኝ። ብረት መቀጥቀጥ በጣም ከባድ ሥራ ነው። ሥራውን እንሠራ የነበረው ከቤት ውጭ ሲሆን አሠሪያችን ይህን ያህል ለሠራተኞች ደኅንነት ደንታ አልነበራቸውም። ደግ የሆነ አሠሪ ለሠራተኞቹ በማሰብ ለሥራ የሚሆን የተሰየ ቤት ይሠራል። እኛ ግን ሜዳ ላይ ነበር የምንሠራው። ቆፈን ሲይዘን ሥራችንን አቁመን በትንፋሻችን

እጃችንን ያሞቅን እንደሆን አሠሪያችን በጣም ይቆጡናል፡፡ 'ለምን የሥራ ጊዜ ታባክናላችሁ' እያሉ ይጮሁብናል፡፡ በተለይ በክረምት ከባድ በረዶ በሚጥልበት ጊዜ ብረት መቀጥቀጥ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ የደረሰበት ያውቀዋል፡፡ ሰውነትን በአጭር ጊዜ አሚምቶ በልጅነት ያስረጃል፡፡ በዚህ ሥራ የተሰማራው ሰው በአርባ ዓመቱ የሰማንያ ዓመት ሽማግሌ ነው የሚመስለው፡፡ እኔ በበኩሌ አምሳ ሦስት ዓመት ከሞላኝ በኋላ ብዙ ጊዜ ያመኝ ነበር፡፡ አሠሪዎች ያረጀ ሽማግሌን መጦር ስለማይወዱ እኔም ላይ ጨከኑ፡፡ ሰው ሲያረጅ 'አርጌ ውሻ' ብለው ነው የሚጠሩት፡፡ በእርጅናዬ ዘመን በቀን ሰላሳ ሱስ ነበር የማገኘው፡፡ ገንዘቡ በጣም አነስተኛ ቢሆንም ምንም ምርጫ ስላልነበረኝ በዚሁ ደመወዝ ሠራሁ፡፡ በዚያን ጊዜ አንዲት ልብስ አጣቢ ልጅ ነበረችኝ፡፡ ይህች ልጅ ልብስ እያጠበች ጥቂት ገንዘብ ታመጣ ነበር፡፡ እርስዋ እየለፋች የምታመጣውን ገንዘብ በማዳመር እየተንገዳገድን እንደማይኖር የሰምና እኛም እንዳትማችን 'ኑሮ ካሉት መቃብርም ይሞቃል' እንዲሉ ኖርን፡፡ እድሜያችንን በዚህ ዓይነት ገፋነው፡፡ ዶፍ ቢወርድ፤ ሐሩር ቢያቃጥል ልጄ ወደኋላ ሳትል ቀኑን ሙሉ ልብስ ታጥባለች፡፡ ልብስ ቶሎ ቶሎ ማጠብ ነበረባት፡፡ አብዛኞቹ ደምበኞችዋ ብዙም ትያሬ የነበራቸው አይደሉም፡፡ ስለዚህ የሚሰጥዋት ልብስ በአለቱ ታጥቦና ተተኩሶ የሚመለስ ነበር፡፡ ጥያቄያቸው ካልተጠበቀ ሁለተኛ ተመልሰው አይመጡም፡፡ የልብስ አጣቢ ሰውነት ከእግር እስከ ጭንቅላት ይርሳል፡፡ ልብሶቹን ታጥብ የነበረው እቤት ሳይሆን ወንዝ ወርዳ ነው፡፡ ከወንዝ የምትመለሰው አንዳንዴ ጀምበር ከጠለቀች በኋላ ነበር፡፡ ወዲያው እንደመጣች መደብዋ ላይ ትዘረራለች፡፡ በጣም ይደክማታል፡፡ ባልዋ እኔ ፊት እንኳን ጠዋት ማታ ይቀጠቅጣታል፡፡ ዛሬ እርስዋ ከዚህ ሁሉ ተገላግላ አንድ ቀን እንኳን ሳይደላት ሞታለች፡፡ መኳንንቶቼ ውሸቴን አይደለም! የምናገረው ነገር ሁሉ እውነት ነው፡፡ እኔ ማን እንደሆንኩ መሴይ ባሉፕን ጠይቁ፡፡ እሁንኑ ሂዱና ጠይቁት፡፡ ከዚህ ይበልጥ ከእኔ ምን እንደምትፈልጉ አላውቅም፡፡፡

ሰውዬው ንግግራቸውን አቆሙ፤ ቁጭ ግን አላሉም፡፡ የተናገሩት በቁጭትና በብሽቀት ነበር፡፡ ንግግራቸውን ሲጨርሱ ከእዚያ የነበረው ሰው ሁሉ ሳቀባቸው፡፡ የሚስቁትን ሁሉ ቀና ብለው ተመለከትዋቸው፡፡ እርሳቸውም ምክንያቱ ምን እንደሆነ ሳያውቁ አብረው ይስቁ ጀመር፡፡

የሚያስፈራና የማይገባ ነገር ነው፤ አይደለም! የመሐል ዳኛው ቅን መንፈስ ያላቸው፤ ለሰው የሚያዝኑ ዓይነት ሰው ነበሩ፡፡ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው «ይህ መሴይ ባሉፕ የተባለውን ሰው ተከሳሹ ቀደም ብሎ የጠቀሰው ስለነበር ተፈልጎ ሊገኝ አልቻለም፡፡ በሥራው ስለከሰረ አገር



ጥሎ ኮብልሎአል» ካሉ በኋላ ወደ ተከሳሹ ዞር ብለው «ቢሆንም ይሻላል፡፡ ሆኖም በመጨረሻ እንድትመልስልኝ የምጠይቅህ ሁለት ጥያቄዎች አሉ፡፡ እነርሱም አንደኛ «ፍራፍሬ ሰርቀሃል ወይስ አልሰረቅህም? ሁለተኛ ከእስር ቤት ያመለጠውና ወንጀለኛው ዣን ቫልዣ ማለት አንተ ነህ ወይስ አይደለህም?»

የሚናገረው ሁሉ እጥርቶ እንደሚያውቅና የተናገሩትን በትክክል የያዘው ሰው እንደሚያደርገው ሁሉ ራሳቸውን ነቀነቁ፡፡ ወደ መሐል ዳኛው ፊታቸውን አዙረው የሚከተለውን ተናገሩ፡፡

«በመጀመሪያ ደረጃ» ካሉ በኋላ ቀና ብለው ጣራውን ከዚያም ከቤቱ ውስጥ የተቀመጠውን ሁሉ ቃኙ፡፡

«ምን ወዲህ ወዲያ ትላለህ? የተጠየቅኸውን መልስ እንጂ፡፡ በራስህ ላይ እኮ ነው የምትፈርደው» አለ ሕግ አስከባሪው፡፡

ተከሳሹ ወዲያው ቀና ብለው በአፋጣኝ ተናገሩ፡፡

«ክፉና ጨካኝ ሰው ነዎት፤ ማለቴ እርስዎ አሁን የተናገሩት፡፡ እኔ የምሠራውንና የምናገረውን አውቃለሁ፡፡ ፍሬ የሚባል ነገር አልሰረቅሁም፡፡ ስርቆት የሚባል ነገርም አይነካካኝም፡፡ የእለት እንጀራ እንኳን የማላገኝ ሰው ነኝ፡፡ ገላዬን ከወንዝ ታጥቤ ስመለስ መንገዱ ሁሉ ጭቃ ሆነብኝ፡፡ ከጭቃው ለመሸሽ ጥግ ጥጉን ስሄድ ፍሬ የያዘ ቅርንጫፍ አየሁ፡፡ የወደቀውን አንስቼ የሞተውን ቅበሩ ነውና አነሳሁት፡፡ ያነሳሁት ይህን ሁሉ መከራና ስቃይ ያስከትልብኛል ብዬ አልነበረም፡፡ አሁን ግን በዚያ ሰበብ ከታሠርኩ ሦስት ወሬ ነው፡፡ ከዚያ ወዲያ የምናገረው ታሪክ የለኝም፡፡ አንተ ታዲያ ክፉ ሰው በመሆንህ ትሰድበኛለህ! በእኔ ላይ ትፈርዳለህ፡፡ የጠባቂዎች ኃላፊ ግን ደግ ሰው በመሆኑ ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብሎ በትህትና 'መልስ ይስጡ እንጂ' እያለ ይመክረኛል፡፡ እኔ እንደሆን ብዙ ባለመማሬና ደሃ በመሆኔ ንግግር አላውቅም፡፡ አሳቤን በቁርጥ ማቅረብ ያሳነኛል፡፡ ሆኖም ቀረም እዚህ ያላችሁት ሁሉ አለመሰረቄን ለማየት ባለመቻላችሁ ተሳስታችኋል፡፡ ስለዣን ቫልዣ ትናገራላችሁ፡፡ እኔ ይህ ሰው ማን እንደሆነ አላውቀውም፡፡ እኔ እሠራ የነበረው ከመሴይ ባሉፕ ዘንድ ሲሆን ስሜ ሻምፕማቲዩ ይባላል፡፡ ንቁ ብትሆኑ ኖሮ የት እንደተወለድኩ ትጠይቁኝ ነበር፡፡ ያም ሆነ ይህ ስለ ራሴ ብዙ አላውቅም፡፡ እያንዳንዱ ሰው የተወለደበት አገር ወይም ቤት ሊኖረው ይችል ይሆናል፡፡ እኔ ግን የት እንደተወለድኩ እንኳን አላውቅም፡፡ እናትና አባቴ ዘላኖች ስለነበሩ የሚኖሩት ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ነበር፡፡ ስወለድ 'ማሙሽ' እያሉ ነበር የሚጠሩኝ፡፡ አሁን ደግሞ 'ሽማግሌው' እየተባልኩ ነው የምጠራው፡፡ አሁን ያሉኝ ስሞች የክርስትና ስሞች ናቸው፡፡

አንተ ደግሞ እንደፈለግክ በላችሁ:: ብቻ እመነኝ እኔ ሌላ ሰው አይደለሁም:: እኔ አባ ሽምጥማትዩ ነኝ:: የናርኩትም ከአሥራዩ ከመስደ ባሉቸ ቤት ነው:: እኔ አሁን የሰለቸኝ እናንተ የምትሉትን ታሪክ መስማት ነው:: ልክ እብድ ውሻ እንደሆንኩ ጓደኝት ሰው ሁሉ እኔን የሚከታተልበት ምክንያት አይገባኝም::»

አቃቤ ሕጉ የመሐል ዳኛን እያየ ተናገረ::

«ጌታዬ፣ ይህ ሰው አላዋቂ በመምሰል የሙሴ ተግባር እየፈጸመ ነው:: ሆኖም የጀመረው የብልጠት ሥራ ፍሬ እንደማያፈራለት አውቃለሁ:: አሁንም የዚህን ሰው ብልጠት ለማክሸፍ የፍርድ ቤቱ መልካም ፈቃድ ከሆነ አራቱ ምስክሮች ተጠርተው እንደገና በአንድነት እንዲመሰክሩበት ይደረግ ዘንድ በአክብሮት እጠይቃለሁ::»

«አቃቤ ሕጉን ለማሳሰብ የምፈልገው ግን የፖሊሱ አዛዥ ዣቬር የምስክርነት ቃሉን ከሰጠ በኋላ አጣዳፊ ሥራ ስለነበረበት ይቅርታ ጠይቆ ሄዷል:: የሄደውም ፍርድ ቤቱ ስለፈቀደለት ነው» አሉ የመሐል ዳኛው::

«እውነት ነው» አለ አቃቤ ሕጉ፤ መሴይ ዣቬር እዚህ ሊገኙ አይችሉም፤ ሆኖም እርሳቸው ለፍርድ ቤቱ ያሰሙት የምስክርነት ቃል በድጋሚ ማሰማት ይቻላል:: መሴይ ዣቬር የተከበሩ ሰው ናቸው:: ሥራቸውን የሚያከብሩና ለእውነት የቆሙ ሰው ናቸው:: ስለዚህ እርሳቸው የሰጡት የምስክርነት ቃል የሚጠራጠሩት አይሆንም:: እርሳቸውም ሲናገሩ «የተከሳሹን ክህደት ለማስተባበል የመሐላ ቃል ወይም የተለየ ማረጋገጫ አያስፈልገንም:: ይህን ሰው በግልጽ ለመለየቱ ጥርጥር የሌለው ነው:: የዚህ ሰው ስም ሽምጥማቲዩ ሳይሆን ወንጀለኛውና እጅግ የሚፈራው ዣን ቫልዣ ነው:: ቱሉን ውስጥ የሚገኘው እስር ቤት ዘቦች አዛዥ በነበርኩበት ጊዜ ሰውዬውን ብዙ ጊዜ አይቼዋለሁ:: ቃሌን እንደገና ብደግም ገና ሳየው ነው ያወቅሁት» ብለዋል::

የዚህ ሰው አነጋገር በዳኞቹና ከዚያ በነበረ ሕዝብ ላይ የማሳመን ኃይል ነበረው:: የመሴይ ዣቬርን የምስክርነት ቃል አስተዋጽኦ ካሰማ በኋላ ከእስር ቤት የመጡት እስረኞች ቃላቸውን በድጋሚ እንዲሰጡና አንዳንድ ጥያቄ እንዲቀርብላቸው አቃቤ ሕጉ ጠየቀ::

የጠባቂዎች ኃላፊ ምስክሮችን በድጋሚ እንዲያስገባ ዳኛው አዘዙ:: ዣን ቫልዣ ከእስር ቤት ከመለቀ በኋላ የእስራት ዘመኑን ጨርሶ የወጣውን ብሬቬት የተባለው ሰው በመጀመሪያ ተጠራ:: ብሬቬት እድሜው ስልሳ ዓመት ነበር::

«ብሬቬት» አሉ ዳኛው፤ «ለመድገም የሚቀፍ የረጅም ጊዜ ቅጣት



ተቀብለሃል፤ ስለዚህ መሐላ ለመማል አትችልም» ሲሉት ብሬቬት አቀረቀረ:: «ሆኖም» በማለት ዳኛው ንግግራቸውን ቀጠሉ፤ «አንድ ሕግ ያዋረደውና ሥራው ያስቀጣው ወንጀለኛ በውስጡ ሌላውን የማክበርና የሌላውን መብት የመጠበቅ ስሜት ይኖረዋል:: ምናልባት ቀደም ሲል በሰጠኸው የምስክርነት ቃል በሕሊናህ ዳኝነት የምታሻሽለው ነገር ቢኖር እንድታሰማን እጠይቅሃለሁ፡ ተከሳሹም ተነስቶ እንዲቆምና መስካሪውም ተከሳሹን እያየ እንዲናገር እንዲሁም ጊዜው በመቆየቱ መስካሪው እስቦና አሰላስሎ አሳቡን እንዲሰጠን እያስታወስኩ ይህ ሰው ቀደም ብላችሁ እስር ቤት ውስጥ አብራችሁ የነበራችሁት ዣን ቫልዣ የሚባል እስረኛ ለመሆኑ አረጋግጠህ በድጋሚ ለመመስከር ትችል እንደሆነ የምስክርነት ቃልህን እንድትሰጥ በድጋሚ እጠይቃለሁ::»

ብሬቬት እስረኛውን አተኩሮ ተመለከታቸው:: ከዚያም ፊቱን ወደ ዳኞቹ አዞረ:: ብሬቬትና ሽምጥማትዩ ዓይን ለዓይን ተፋጠጡ::

«አዎን ጌታዬ! ይህ ሰው ዣን ቫልዣ ለመሆኑ በመጀመሪያ የለየሁት እኔ ነኝ:: አሁንም ቢሆን ቃሌን አልለውጥም:: ይህ ሰው ዣን ቫልዣ ራሱ ነው:: ቱሉን ከሚገኘ ወህኒ ቤት የገባው በ1796 ዓ.ም ሲሆን ከዚያ ያመለጠው በ1815 ዓ.ም. ነው:: እኔ ከእስር ቤት የወጣሁት እርሱ ባመለጠ በዓመቱ ነበር:: ሰውዬው አሁን ሲያዩት በመጠኑም ቢሆን ሰውጥ አለው:: ግን ይህ ከእድሜ ጋር የሚሄድ በመሆኑ ያሳየው ለውጥ ሊያሳስተኝ አይችልም፤ ዣን ቫልዣ ራሱ ነው::»

«ቁጭ በል» አሉ ዳኛው:: ተከሳሹ ግን እንደቆመ ይቆይ::

ሽኒልዲዩ የሚባል ምስክር እንዲገባ ተደረገ:: ቱሉን ውስጥ ከሚገኝ እስር ቤት የእድሜ ልክ እስረኛ ነው:: የምስክርነት ቃሉን እንዲሰጥ ነው ከእስር ቤት የተጠራው:: ቁመቱ አጠር ያለ የሃምሣ ዓመት አዛውንት ነው:: ምንም እንኳን ፊቱ የተጨማደደ ቢሆንም በሁኔታው ነቃ ነቃ ያለና ተቅበጥባጭ ሰው ነው::

ዳኛው ለብሬቬት ያሉትን ለእርሱም ደገሙለት:: «በሥራኸው ወንጀል የተነሣ በመማል ቃልህን ታከብራለህ ለማለት ስለማያስደፍር መማል አትችልም» ሲሉት ሽምጥማቲዩ ቀና ብለው ተመልክተው ከዚያ የነበረውን ተመልካች በዓይን ቃኙት:: ዳኛው አሳቡን እንዲሰበስብና እስረኛውን በትክክል ያስታውሰውና ያውቀው እንደሆን ጠየቁት::

ሺኒልዲዩ ከት ብሎ ሳቀ::

«ታውቀው እንደሆን አሉኝ! አምስት ዓመት ሙሉ በአንድ ሰንሰለት አብ ነው ታስረን የነበረው:: አንተ በአንድ ብረት ታስረን አልነበረም?»